ወርኃዊ ጥንቅር፣ ቁ.012
ጥር 2018 ዓ.ም



# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

እንደራሴ

እንደራሴ በብርጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

research@bridge-et.org

## መልክዓ - ብሪጅ

መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው :: ብሪጅ፣ በዋናነት በኢትዮጵያ እና በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል አገራት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እንዲጎለብት እና ሰላም እንዲበለጽግ የሚሠራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፖሊሲ ተኮር የጥናት እና ምርምር ተቋም ነው ::

## ተልዕኮ

ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ይጎለብት ዘንድ፣ ለፖሊሲ አወጣጥ ግብዓት የሚሆኑ፣ ተጨባጭነት ያላቸው ምርምሮችን ማድረግ እና የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ፤

## ርዕይ

በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች እና በቀጠናዊ የሰላም፣ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰዋዊ እና ቁሳዊ ልማት ላይ፣ በኢጋድ ቀጠና ተቀዳሚ የምርምር እና ፖሊሲ አመንጪ ማዕከል መሆን፤

## መሠረታዊ ዕሴቶች

- አጽንዖተ ትኩረት፡- ከፍተኛ ትኩረት የተሰሩ እና ተጨባጭነት ያላቸው ጥናት ምርምሮችን ማቅረብ።
- አዲስነት፡- ለዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ተግዳሮቶች ፈጠራዊ እና ተለዋዋጭ መፍትሔዎች የታከለባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዋጣት
- ታማኝነት፡- ተዓማኒነት ያላቸውን የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ ተዓማኒነትን መጠበቅ

## ግቦች

ኢትዮጵያ እና በኢጋድ ቀጠና የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል ፓርላማዎች በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር

- ተጨባጭ ምርምሮችን መከወን
- የእንደራሴዎችን ብቃት ለማሳደግ የዐቅም ግንባታ ድጋፎችን ማድረግ
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ክንውኖችን መከታተል

BRIDGE Research & Innovation - Parliaments. Peace. Policy

+251 99 808 5013

+251 115 57 74 96

info@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

UNECA, SA Building, 9th Floor,

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.

# ማውጫ


የኢትዮጵያ እንደራሴዎች የወርኃ ጥር ክራሞት ........ 2

1. በወሩ የተካሄዱ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባዎች........ 2

2. የጠቅላይ ሚኒስትሩ ውሎ በፓርላማ........ 3

“አዲሱ የታሪክ ምዕራፍ” ........ 3

“ኢትዮጵያ ምንም ዓይነት ኮሜርሺያል ብድር አልተበደረችም” ........ 4

“አኹን የቸገረን የወልቃይት አካባቢ ነው”........ 6

“ጾቡ የተጀመረው...” ........ 8

3. የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት........ 11

3.1 የጸደቁ ሕግጋት ........ 11

3.2 ረቂቅ ሕግጋት........ 12

3.3 አስረጂ መድረኮች........ 13

4. የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር........ 15

4.1 የተቋማት ሪፖርቶች........ 15

4.2 የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች ........ 19

4.2.1 የተቋማቱ ጉብኝቶች........ 19

4.2.2 የመስክ ጉብኝቶች........ 21

5. የፓርላማ ዲኘሎማሲ ........ 27

6. እንደራሴዎቹ ስለ‘ራሳቸው በ‘ራሳቸው........ 29

7. እንደራሴዎቹ እና ምርጫ 2018........ 31

8. ሹመቶች........ 33

9. የብሪፊ ዳሰሳዊ ምልከታ በሽግግር ፍትሕ፣ በእንደራሴዎቹ ሚና እና ተያያዥ ርዕሰ-ጉዳዮች ዙሪያ ........ 34

የሽግግር ፍትሕ ሲሉ... ........ 34

ለመሆኑ ፖሊሲው ምን ይዟል? ........ 36

ዘገየ ይሆን? ........ 38

ከሥርዓተ- ጾታ አንጻርስ? ........ 39

ሒሳዊ ትችቶችስ ምን ያነሳሉ? ........ 41

የብሪፊ ምክረ ሐሳቦች........ 43

## የኢትዮጵያ እንደራሴዎች የወርኃ ጥር ክራሞት

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በወርኃ ጥርም የተለያዩ ሕገ-መንግሥታዊ እና ተቋማዊ ኀላፊነቶቻቸውን ከውነዋል። በወሩ ውስጥ ሦሥት መደበኛ ስብሰባዎችን ሲያደርጉ፣ የአገሪቷን ርዕሰ-መንግስት የበጀት ዓመቱን የስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ተከትሎ የተለያዩ ጥያቄዎችን እና ማብራሪያ ያሻቸዋል ያሏቸውን አገራዊ ጉዳዮች አንስተው፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ምላሾች አድመጠዋል። ከዚያ ባለፈም፣ ዐዋጆችን አጽደቀዋል፤ ረቂቅ ሕግጋትንም ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች መርተዋል። ይኽች የእንደራሴ የቅጽ አንድ የመጨረሻ ዕትምም፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ዋንኛ ማብራሪዎች፣ የጸደቁትንም ሆነ በረቂቀ ደረጃ የተያዙትን ይዛ፣ የሥራ አሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥሮችን እና የተቋማት እና የመስክ ምልከታዎችንም አዳብላ፤ ለወሩ የመረጠችውን የሽግግር ፍትሕ እና የእንደራሴዎቹን ሚና ርዕሰ-ጉዳይ አስተሳስራ እንዲኽ ቀርባለች።

## 1. በወሩ የተካሄዱ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባዎች

| 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን | ቀን | አጀንዳ |
|---|---|---|
| **9ኛ መደበኛ ስብሰባ** | ጥር 14 | * በኢትዮጵያ፣ በሕዝባዊት ሪፐብሊክ ቻይና በብራዚል እና በደቡብ አፍሪካ መንግሥታት መካከል የወንጀል ጉዳዮችን አሳልፎ መስጠትን የተመለከቱ ዐዋጆችን ማጽደቅ፤<br>* የጤና ተቋማትን አገልግሎት እና ተደራሽነትን ለማሻሻል የሚያግዝ የብድር ስምምነትን ለዝርዝር ዕይታ መምራት፤<br>* የኅብረት ሥራ ማሻሻያ፣ የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኩዩሪቲን ለማሻሻል የቀረበን እና የፌዴራል የስፖርት ልማት እና አሥተዳደር ረቂቅ ዐዋጆችን ለዝርዝር ዕይታ መምራት፤ |
| **10ኛ መደበኛ ስብሰባ** | ጥር 25 | * የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ፣ በፌደራል መንግስት የ2018 በጀት ዓመት የ6 ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ከእንደራሴዎቹ ለሚቀርቡላቸ ጥያቄዎች የሚሰጧቸውን ምላሾች እና ማብራሪያዎች ማድመጥ፤ |
| **11ኛ መደበኛ ስብሰባ** | ጥር 27 | * የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን አጩ የቦርድ አባላትን፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አጩ ምክትል ፕሬዚዳንቶችን እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አጩ ዳኞችን ሹመት ማጽደቅ፤ |

## 2. የጠቅላይ ሚኒስትሩ ውሎ በፓርላማ

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ ወርኃ ጥርን ያገባደዱት ሕግ በማውጣት አልያም ተቋማትን በመቆጣጠር እና የመስክ ጉብኝት በማድረግ ብቻም አልነበረም፤ ከዚያ አለፍ ብለውም፣ የአገሪቷ ርዕሰ-መንግሥት የዚኽኑ በጀት ዓመት የመንፈቅ የሥራ አፈጻጸም በማድመጥ እና ከሪፖርቱም ሻገር ያሉ ማኅበረ-ፖለቲካዊ እና ዲፕሎማሲ ተኮር ጥያቄዎችን አንስተው ምላሽ እንዲሰጧቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩን በመጠየቅም ነበር።



*ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ የ6 ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት*

እንደራሴዎቹ ካነሷቸው ጥያቄዎች መካከል፤ ከሰላም እና ጸጥታ እስከ የተፈናቃዮች አኹናዊ ኹኔታ፣ ከኑሮ ውድነት እስከ የባሕር በር ሰንባች ጥያቄ፣ ከቀጣዩ 7ኛ ጠቅላላ ምርጫ እስከ የኤርትራ ጉዳይ ያሉት በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉት ናቸው። የጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድን የትናንትናውን የእንደራሴዎች ምክር ቤት ውሎን ዋንኛ ነጥቦችም፣ እንደራሴ እንደሚከተለው በንዑስ ርዕሳት አዋቅራ አጠር አድርጋ አጠናቅራቸዋለች።

### "አዲሱ የታሪክ ምዕራፍ"

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ፣ በፓርላማው ውሏቸው በትምህርት እና ተያያዥ ማኅበራዊ የመንግስታቸው ፖሊሲዎች ዙሪያ ዘርዘር ያሉ ነጥቦችን አንስተዋል። በትምህርት ዘርፍ ጥራት ያለው ትምህርት በፍትሓዊነት የማድረስ ሥራ እየተሰራ መሆኑን አስቀድመው የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የትምህርት ጥራትን በዘላቂነት ለማረጋገጥ ታችኛው ትውልድ ላይ በማተኮር መሥራት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፤ ለዚህም ወደ 34ሺ መዋዕለ ሕጻናት ተገንብቶ የነገ የአገር ተረካቢዎቹ ሕጻናት እየተማሩ መሆኑን ገልጸዋል።

በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ደረጃን የማሻሻል፣ የመምህራን ዐቅምን የማጎልበት፣ የተማሪዎችን የቴክኖሎጂ ዕውቀት እና ክህሎት የማሳደግ ሥራዎችም ተጠናክረው እንደሚቀጥሉም ተናግረዋል። የጤናውን ዘርፍ በተመለከተ ኹሉን ዓቀፍ የጤና ተደራሽነት እና ጥራት ለማሳደግ ልዩ ትኩረት በመስጠት በመከላከሉ እና አክሞ የማዳን ተግባራትን በማቀናጀት በርካታ ሥራዎች መከናወናቸውን የጠቀሱት የተከበሩ ዶ.ር. ዐቢይ፣ በዘርፉ በተሰራው ማሻሻያ ውጤት የተገኘ ቢሆንም ብዙ ሥራ ይጠይቃል ሲሉ ተደምጠዋል። በማሳያነት ያነሱት በጤና ተቋማት የሚወልዱ እናቶች 63 በመቶ መድረሱን እና የሚሞቱ እናቶች ቁጥርም መቀነሱን ሲሆን፤ ከጥቂት ወራት በፊት ተከስቶ የነበረው የማርበርግ በሽታን ሦሥት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መቆጣጠር መቻሉንም በማሳየነት አክለው ጠቅሰዋል።

የነገውን ብርቱ ውድድር ለማሸነፍ የዛሬው ዝግጅት ወሳኝ መሆኑን ለእንደራሴዎች ሲናገሩ የተደመጡት የገዢው

ፓርቲ ፕሬዝደንት፣ ወጣቶችን ለላቀ ስኬት ለማብቃት መንግስት በትኩረት እየሰራ መሆኑንም ረገጥ አድርገው ሲናገሩ ተስተውለዋል። ከአገሪቱ አምስት የዕድገት ምሰሶዎች መካከል አንዱ ቴክኖሎጂ እንዲሆን መደረጉ ለትውልድ የተሰራ ትልቅ መዋዕለ-ንዋይ መሆኑን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በተለይም በሰው ሰራሽ አእምሮ ረገድ ኢትዮጵያ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ እየከፈተች መሆኗን አብራርተዋል። በዚህም መሠረት ኢትዮጵያ በዓለም ኹለተኛ የሆነውን ግዙፍ የሰው ሰራሽ አእምሮ ዩኒቨርሲቲ ለመገንባት በከፍተኛ ፍጥነት እየሰራች ሲሆን፣ ይኽ ታላቅ የትምህርት ተቋም በሚቀጥለው አንድ ዓመት ውስጥ ሥራ እንደሚጀምርም ተናግረዋል። አባቶቻችን የኢትዮጵያ አየር መንገድን ገንብተው በዓለም ስመ-ጥር እንዳደረጉት ኹሉ፣ ይኽ ዩኒቨርሲቲም ለኢትዮጵያ ልጆች የተሻለ ዘመንን እና ብሩህ የወደፊት እድልን ይዞ ይመጣል ሲሉ ተስፋቸውን ለእንደራሴዎቹ አጋርተዋቸዋል።

## “ኢትዮጵያ ምንም ዓይነት ኮሜርሺያል ብድር አልተበደረችም”

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ፣ በምክር ቤቱ ውሏቸው፣ ዘለግ ያለ ማብራሪያ ከሰጡባቸው ጉዳዮች ቀዳሚው፣ ከዓመት ከመንፈቅ አንስቶ መንግስታቸው የተከተለውን የዐብይ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ውጤቶችን በቁጥራዊ መረጃዎች ጭምር አስደግፈው ያብራሩበት ኢኮኖሚ ተኮሩ ርዕሰ-ጉዳይ ነበር። የኢኮኖሚው ማሻሻያ ዋንኛ ዓላማዎች፣ የዐብይ ኢኮኖሚ ስብራቱን ማረጋጋት፣ የኢኮኖሚ አቅጣጫዎችን ከግብርና መር ወደ ብዝሓ ዘርፍ ማሸጋገር እና የአገሪቷን የእዳ ጫና ማቃለል መሆናቸውን የጠቀሱት ጠቅላዩ፣ በኹሉም መመዘኛ በኢትዮጵያ አመርቂ የኢኮኖሚ ስኬት ተመዝግቧል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የኑሮ ውድነት እና የዋጋ ግሽበት፣ የሥራ አጥ ቁጥር መበራከት እና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች በኢኮኖሚው እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደራቸውን በተመለከተ እንደራሴዎቹ ላነሱላቸው ጥያቄዎችን ሲመልሱም፤ በአገሪቱ የዋጋ ግሽበትን እና የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት ዘርፈ-ብዙ ተግባራት የተከናወኑ መሆናቸውን በማስታወስ፣ ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍም ምርት እና ምርታማነትን የበለጠ ማሳደግ እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል። የኑሮ ውድነትን እና የዋጋ ግሽበትን ለመቀየር በቀጣይ በምግብ ማምረት፣ በቤት ግንባታ፣ በትራንስፖርት እና በትምህርት ቤት የተማሪዎች ምገባ ዘርፎች ላይ መንግስት የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ መሆኑንም ለምክር ቤቱ አባላት ጠቅሰውላቸዋል። በ2018 በጀት ዓመት ባለፉት ስድስት ወራት በአገር ውስጥ ለ2.6 ሚሊየን ዜጎች የሥራ እድል የተፈጠረ ሲሆን፣ በውጭ አገራት ደግሞ ከ350 ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን የሥራ እድል የተመቻቸላቸው መሆኑም ተሰምቷል።

በኢትዮጵያ የኑሮ ውድነት እና የዋጋ ግሽበት፣ የሥራ አጥ ቁጥር መበራከት እና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች በኢኮኖሚው እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደራቸውን በተመለከተ እንደራሴዎቹ ላነሱላቸው ጥያቄዎችን ሲመልሱም፤ በአገሪቱ የዋጋ ግሽበትን እና የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት ዘርፈ-ብዙ ተግባራት የተከናወኑ መሆናቸውን በማስታወስ፣ ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍም ምርት እና ምርታማነትን የበለጠ ማሳደግ እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል። የኑሮ ውድነትን እና የዋጋ ግሽበትን ለመቀየር በቀጣይ በምግብ ማምረት፣ በቤት ግንባታ፣ በትራንስፖርት

እና በትምህርት ቤት የተማሪዎች ምገባ ዘርፎች ላይ መንግስት የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ መሆኑንም ለምክር ቤቱ አባላት ጠቅሰውላቸዋል። በ2018 በጀት ዓመት ባለፉት ስድስት ወራት በአገር ውስጥ ለ2.6 ሚሊየን ዜጎች የሥራ እድል የተፈጠረ ሲሆን፣ በውጭ አገራት ደግሞ ከ350 ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን የሥራ እድል የተመቻቸላቸው መሆኑም ተሰምቷል።

ባለብዝሓ-ተዋናይ የኢኮኖሚ ዘርፍ ዕድገትን በመከተል በግብርናው እና በኢንዱስትሪው እንዲኹም በሌሎች ንዑስ የኢኮኖሚ ዘርፎች አመርቂ ውጤት እየተገኘበት ያለ በጀት ዓመት መሆኑን ሲያነሱም፣ መንግሥት በበጀት ዓመቱ 9.2 የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ አቅዶ በሠራቸው ውጤታማ አመላካች ሥራዎች በዓመቱ ማጠቃለያ 10.2 ጥቅል አገራዊ ዕድገት ለማስመዝገብ በትኩረት እየሰራ መሆኑን ጠንከር አድርገው ሲናገሩ ተደምጠዋል። ለዚህም በበጀት ዓመቱ ለሚመዘገበው ጥቅል አገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት የመንግስት እና የዓለም ዓቀፉ የገንዘብ ተቋም (አይኤምኤፍ) አመላካቾች ተቀራራቢ መሆናቸውንም አስታውሰዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ ኢኮኖሚውን አስመልክቶ በጠነከረ ድምጸት ከተናገሩባቸው ጉዳዮች አንዱ፣ ኢትዮጵያ ምንም ዓይነት ኮሜርሻል ብድር አልተበደረችም ያሉበት የንግግራቸው ክፍል ነው። 'ርሳቸው ወደ ሥልጣን ከመጡ ወዲኽ ኢትዮጵያ ምንም ዓይነት ኮሜርሻል ብድር እንዳልተበደረች ያነሱት ጠቅላዩ፣ ከለወጡ በፊት ኢትዮጵያ በጣም ብዙ ብድር እንደነበረባት እና አበዳሪ አገራት ኢትዮጵያ መክፈል አትችልምና አናበድርም ያሉበት ኹኔታ እንደነበረም አንስተዋል። ኢትዮጵያ ላለፉት ሃያ ዓመታት ለፕሮጀክቶች በሚል ሰበብ ጤነኛ ያልሆነ የብድር ስምምነት ወይንም ኮሜርሻል ብድር ከአንዳንድ አገራት በመበደር ለመክፈል ሳትችል መቅረቷንም ለእንደራሴዎቹ አስታውሰዋቸዋል።

ኢትዮጵያ ብድር መበደር የማትችል የሚል ታርጋ ተሰጥቷት እንደነበር ያስታወሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የተካሄደው የኢኮኖሚክ ማሻሻያ ይኽንን አሻሽሏል ብለዋል። ባለፈው ዓመት ዐሥር ፈጣን ዕድገት ከተመዘገበባቸው የዓለም አገራት መካከል አምስቱ አፍሪካውያን ናቸው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያ ከቀዳሚዎቹ አንዷ ናት ሲሉም በቀጥታ በተላለፈው ንግግራቸው ሲያወሱ ተደምጠዋል።



***እንደራሴዎቹ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ማብራሪያ ሲያደምጡ***

ኢትዮጵያ ባለፉት ስድስት ወራት በኢኮኖሚው መስክ አስገራሚ መነቃቃት እያሳየች መሆኑን ሲናገሩም በማሳያነት ያነሱት፣ አገሪቷን አኹን ያላትን የውጪ ምንዛሬ ክምችት ነበር። መንግሥት የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር በቢሊየኖች የሚቆጠር ድጎማ እያደረገ መሆኑንም ጠቅሰው፣ አገሪቱ ባለፉት ስድስት ወራት በታሪክ የመጀመሪያ የሆነ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ገቢ አግኝታለች ብለዋል። በዚህም መሠረት ከሸቀጦች ንግድ 4.5 ቢሊየን ዶላር፣ ከአገልግሎት ዘርፍ 4.6 ቢሊዮን ዶላር፣ ከውጭ

ሃዋላ 2.3 ቢሊየን ዶላር እንዲኹም ከውጭ ቀጥታ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት ከ2 ቢሊየን ዶላር በላይ ተገኝቷል ብለዋል። በዚኽ የተነሳም፣ የአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ክምችት በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ ወደማይታወቅ ከፍተኛ ደረጃ መድረሱን ተናግረዋል።

የብልጽግና ፓርቲው ፕሬዝደንት የዐብይ ኢኮኖሚ ማብራሪያቸውን በቁጥሮች አስደግፈውም ሲያብራሩ ተደምጠዋል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ በለውጡ ጊዜ 8 ሚሊየን ሰዎችን በዓመት ያጓጉዝ እንደነበር እና ባለፉት ስድስት ወራት ግን 10 ነጥብ 7 ሚሊየን ሰዎችን ማጓጓዙን አንስተው፣ ዘንድሮ ደግሞ ቁጥሩ 22 ሚሊየን ይደርሳልም ብለዋል። በለውጡ ሰሞን 37 ሚሊየን ሰው ሞባይል ይጠቀም ነበር ያሉት ዶ.ር. ዐቢይ፣ አኹን ላይ ከ97 ሚሊየን ሰው በላይ ሞባይል እንደሚጠቀም ጠቅሰዋል። ቁጥራዊ ማብራሪያቸውን ሲለጥቁም፣ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ሲጀመር 48 በመቶ ያመርቱ የነበሩ ኢንዱስትሪዎች 66 ነጥብ 3 በመቶ መድረሳቸውን ጠቅሰው፣ ‘ርሳቸው ሪፖርት ባቀረቡበት የጊዜ ሽፋን ውስጥ ባሉት ስድስት ወራት የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪዎች የኃይል አጠቃቀም ብቻ 16 በመቶ አድጓል ብለዋል።

ከኢንዱስትሪው በመለስ በማዕድን ነውስ የኢኮኖሚ ዘርፎችም ከፍተኛ ያሉትን ዕድገት መንግስታቸው ማስመዘገቡን ሲያብራሩ፤ የብረት ምርት 36 በመቶ፣ የሲሚንቶ ምርት ደግሞ 28 በመቶ ጨምሯል ብለዋል። ሰሞነኛው የመካከለኛው ምሥራቅ ውጥረት የነዳጅ ዋጋን ከፍ እና ዝቅ እያደረገው እንደሚገኝ ለእንደራሴዎቹ ያስታውሱት ርዕሰ-መንግስቱ፣ መንግስታቸው ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል የነዳጅ ዋጋ የቀየረው ሰባት ጊዜ ብቻ መሆኑን ጠቅሰው፣ በየቀኑ ሲጨምር ዋጋውን ከተጨመረ ሕዝባችን ይጎዳል በሚል ይኽ አለመደረጉን ተናግረዋል።

የቀደመውን የዓመት ከመንፈቅ የዐብይ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ፣ የባሕር ማዶ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ መግባት ሀገር-በቀሎቹን ይጎዳ ይሆን በሚል ዙሪያ ከእንደራሴዎቹ ለቀረበላቸው ጥያቄም፣ ባንኮች ባንክ መሆን ባለባቸው ደረጃ የማደግ ሂደታቸው በውድድር መታጣት ምክንያት ውስንነት ገጥሞታል ሲሉ ምላሻቸውን ጀምረዋል። ላለፉት ሣሥት ዐሥርታት የኢትዮጵያ ባንኮች ያለ ውድድር ብቻቸውን እንዲሰሩ መደረጉንም በማንሳት፣ የውጭ ባንኮች ቢገቡ ካፒታል እና ቴክኖሎጂ ስለሚያመጡ ለአጠቃላይ እድገት ብቻም ሳይሆን፣ የእኛንም ፋይናንሻል ሴክተር የማሳደግ ሚና ይኖራቸዋል ሲሉ የመንግስታቸውን አኹናዊ አቋም አብራርተዋል። “እኛ ስላለቀቀን የድሮ በሽታ በጣም በትንሹ ነው የከፈትነው እንጂ ያን ያህል የእኛንም ባንኮች በሚያጠፋ መንገድ የተከፈተ አይደለም” ሲሉም፣ የንውስ ኢኮኖሚው ለባሕር ማዶ ባንኮች መከፈት አገራዊ ጉዳት እንደማያስከትል አጽንዖት ሰጥተው ሲናገሩ ተሰተውለዋል።

## “አኹን የቸገረን የወልቃይት አካባቢ ነው”

ሰፋ ያለ የማክሰኞ ማለዳ ሰዐታቸውን በኢኮኖሚው ዙሪያ ያደረጉት ጠቅላዩ፣ ከዚያ ማብራሪያቸው ለጥቀው የአገር ቤቱን ፖለቲካ አስመልክቶ በተነሱላቸው ጥያቄዎች ዙሪያ ሰፋ ያሉ ማብራሪያዎችንም ሰጥተዋል። ከጥንት እስከ ትናንት የኢትዮጵያ የሰላም እጦት ችግሮች ከሣሥት በኩል እንደሚነሱ ቀደም ብለው የጠቀሱት የአገሪቷ ጠቅላይ ጦር አዛዥ፣ አንደኛው ከጥንት የተጠባነው ልዩነቶቻችን በኃይል ብቻ የመፍታት ልምምድ ነው ሲሉ ተሰምተዋል። ከጥንት

የመጣ ያሉት የባንዳነት ልምምድን በኹለተኛነት ጠቅሰው፣ ሦሥተኛው የጠላቶቻችን ኢትዮጵያ ካደገች የሚል ያልተቋረጠ ስጋት ሲሉ መነሾዎች ያሏቸውን ጠቅለል አድርገው በማንሳት ወደ ቀሩት ፖለቲካ ተኮር ማብራሪያዎቻቸው ተሻግረዋል።

“አልጋ አካልን፤ ውይይትም ልብን ያሳርፋል” ያሉት የተከበሩ ዶ.ር. ዐቢይ፣ መወያየት ብዙ ስብራቶችን እንደሚጠግንም ተናግረዋል። የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ በርካታ ኢትዮጵያውያንን ማወያየቱን እና አጀንዳ ማሰባሰቡን በመጥቀስም፣ ውይይቱ ለኹሉም ክፍት ነው ሲሉ፣ በተሰበሰቡ አጀንዳዎች ፍላጎቶቻችን ተቀራራቢዎች ናቸው ነው ሲሉም ተደምጠዋል።

"ባንዳነት ያቆስላል እንጂ አይገድልም” ሲሉ በበካር ድምጽ የተናገሩት ጠቅላዩ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ዘላቂ ሠላም እንዳይሰፍን ምክንያት የሆነው በባንዳ እና በባዳ የቅንጅት ተግባር መሆኑን ገልፀዋል። ወደ ነጠላ ፖለቲካዊ ርዕሰ-ጉዳይ ሻገር ብለውም፣ የወልቃይትን ጉዳይ ያነሱት ዶ.ር. ዐቢይ፣ “የወልቃይትን ጉዳይ እኔም እናንተም አትወስኑም፤ የሚወስነው የዚያ አካባቢ ሕዝብ ነው" ሲሉ በዕለተ-ማክሰኞቹ ውሏቸው ላገኟቸው እንደራሴዎች ነግረዋቸዋል። ሰፋ ባለው የዚኹ የወልቃይት ንግግራቸው፣ “የተፈናቀሉ ሰዎች መመለስ ይፈልጋሉ፤ ቀድመው የነበሩበት አካባቢም ይምጡልን ይላሉ፤ ማነው የያዛቸው ነው ጉዳዩ” ሲሉም ማብራሪያቸውን መጥይቃዊ ምላሽ አክለውበታል።

ከዚያ ባለፈም፣ “በራያ አይታችኋል፤ ሰው ተመልሷል እየኖረ ነው። በጸለምት አይታችኋል፤ ሰው ተመልሷል እየኖረ ነው። ብዙው ኦሮሚያ አካባቢ ተመልሷል እየኖረ ነው። የቸገረን አሁን የወልቃይት አካባቢ ነው።” ሲሉ የተደመጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ፣ “ሰዎቹ መመለስ ስለማይፈልጉ ሳይሆን፣ ተፈናቃይን መያዝ ያደረገ ፓለቲካ ኢትዮጵያ ውስጥ በመኖሩ ነው” ሲሉም ምክንያት ያሉትን አስቀምጠዋል። የኔ ቢጤዎች ልጆቻቸውን መለመኛ እንደሚያደርጉት፣ አንዳንድ ፓርቲዎች ተፈናቃይን የራስ ህልውና ማቆያ ያደርጓቸዋልም ብለዋል። በወልቃይት ጉዳይ መንግስታቸው የያዘውን አቋም ሲያስረዱም፣ “ፌደራል መንግስት እያለ ያለው ሰው አይፈናቀል፤ ወደነበረበት ይመለስ፤ ራሱን ያስተዳድር ራሱ ይወስነው ነው። አንድ ሰው እዚህ ተቀምጦ ከሚወስን በሪፈረንደም፣ በሕጉ አግባብ ይወሰን ነው” ሲሉም ተሰምተዋል።

ትግራይን የሚነካውን የወልቃይትን ጉዳይ እያይዘው ወደ ትግራይ ፖለቲካ የዞሩት የተከበሩ ዶ.ር. ዐቢይ፣ የትግራይ ሕዝብ አሁን ካለበት ችግር ወጥቶ ራሱ ተግቶ ሠርቶ መለወጥ የሚፈልግ ሰላም ወዳድ ሕዝብ ነው ሲሉ ተደምጠዋል። የትግራይ ሕዝብ ሰላም፣ ልማት ይፈልጋል፤ ከሌሎች ወንድም ኢትዮጵያውያን ጋርም በጋራ መሥራት እና ማደግ ይፈልጋል ያሉት ዶ.ር. ዐቢይ፣ ነገር ግን የትግራይ ሕዝብ በፖለቲካ አውድ ውስጥ መድረክ እንጂ ተዋናይ መሆን አልቻለም፤ መድረኩን ሌሎች ይጫወቱበታል እንጂ ራሱ አይጫወትም ብለዋል። በትግራይ ያሉ ፖለቲከኞችም ከአጃቢ ተዋንያን ወደ መሪ ተዋንያን መሸጋገር እንዳለባቸው አመላክተው፣ ለዚኽ ደግሞ አዲስ የፖለቲካ አስተሳሰብ እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት 10ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ፣ በቀጣዩ 7ኛ ብሔራዊ ምርጫ ዙሪያም ጥያቄ ተነስቶላቸው ምላሽ ሰጥተዋል። የዘንድሮው ምርጫ ከቀደሙት የተሻለ

ይሆናል ሲሉ የተደመጡት የብልጽግናው ፕሬዝደንት፣ የዘንድሮው ምርጫ ሰላማዊ፣ ፍትሓዊ እና አካታች ለማድረግ እየተሰራ መሆኑንም ተናግረዋል። ባለፉት ዓመታት ከተካሄዱት ምርጫዎች የተሻለ እንዲሆን አበክረን ነው እየሰራን ያለነው ሲሉም አክለዋል።

የመንግሥት ኃላፊዎች በተለያዩ ክልሎች ተንቀሳቅሰው እየሰሩ መሆኑን የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ አሁን እኔ የተሻለ ምርጫ ይኖራል እያልኩ ነው፤ አንዳንዶች ሰግተዋል፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መልሱ በውጤት እንየው ነው ሲሉም ተደምጠዋል። ምርጫው ባለፈው ከነበረው ምርጫ አሳታፊ እንዲሆን ይሰራል በማለትም፣ "የአንድ ፓርቲ ድምጽ ለኢትዮጵያ አይጠቅማትም" ብለዋል። አክለውም የኔ እምነት ይኽ ፓርላማ አኹን ካለው የአምስት እና የዐሥር ሰዎች ድምጽ፣ በአምስት እና ዐሥር እጥፍ ያድጋል የሚል እንደሆነ ተናግረዋል።

ከቀጣዩ የ2018 ምርጫ ባለፈም፣ የኢትዮጵያ አየር ኃይልን ጉዳይ በፖለቲካ ተኮሩ የማብራሪያቸው ክፍል ያነሱት ጠቅላይ ጦር አዛዡ፣ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ደረሰበት ያሉትን የጥንካሬ ደረጃ ይፋ አድርገዋል። በለውጡ መጀመሪያ አንድ መብረር የሚችል ሄሊኮፕተር ብቻ የነበረው አየር ኃይላችን፣ ዛሬ ላይ የተለያየ ስም እና ተግባር ያላቸው ከ100 በላይ ዘመናዊ አውሮፕላኖች ባለቤት ሆኗል ሲሉም ማብራሪያቸውን በቁጥሮች ጭምር አስደግፈዋል። ዝግጅቱ የአገርን ምሰሶ የሚገዳደሩ ኃይሎች ከመጡ ኢትዮጵያን ለማጽናት እና ለማስቀጠል የታለመ የጥንካሬ መገለጫ መሆኑን ያነሱት አዛዡ፣ ከባንዳዎች የበለጠ ሀብት ካላመነጨን በስተቀር በሚዲያ እና በዲፕሎማሲ ጫና ይፈጠራል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ መፍትሔው ብቃትን በማጎልበት ጠንክሮ መገኘት መሆኑን አሳስበዋል።

## "ጸቡ የተጀመረው..."

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ፣ በምክር ቤቱ የግማሽ ቀን ውሏቸው፣ ከማኅበረ-ፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ተኮር የስድስት ወራት የመንግስታቸው ውጤቶች እና ቀጣይ ዕቅዶች ባለፈም፣ በዲፕሎማሲው እና በቀንዱ ዙሪያም ጠንከር ያሉ ነጥቦችን በማብራሪያቸው ላይ አንስተዋል። የሕዳሴ ግድብን አስመልክቶ፣ ከሳምንት በፊት ከአሜሪካው ፕሬዝደንት ዶናልድ ትራምፕ በኩል ለተሰማው ንግግር ጠቅላዩ ጠንካራ ምላሽ ሰጥተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያ በሕዳሴ ግድብ ግንባታ ወቅት አንድም ብድር እና እርዳታ ከየትኛውም ወገን አለመውሰዷን ተናግረዋል። "በጀግኖች ኢትዮጵያውያን ቁርጠኛ አቋም፣ በአገርም ውስጥ ከአገር ውጪም ባሉ ኢትዮጵያውያን በቁርጠኝነት ጨክነው በጋራ ቆመው ስለሠሩ የተከወነ ፕሮጀክት ነው" ሲሉ ለግድቡ ግንባታ ብድርም ሆነ እርዳታ አገሪቷ እንዳልወሰደች አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ አገራቸው የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታን በገንዘብ መደገፏን በቅርቡ በተደጋጋሚ ሲናገሩ የቆዩ ሲሆን፣ ይህንን ተከትሎ የጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ ምላሽ በከፍተኛ የአገሪቷ መሪ ደረጃ የተሰጠ ይፋዊ መልስ ሆኗል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክለውም፣ ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ቀዳሚ የሆነውን ታላቁን የሕዳሴ ግድብ ገንብታ ብቻ እንዳልቆመች በመግለጽ፣ ከአፍሪካ ሦስተኛ የሆነውን ኮይሻን እየሠራች ነው ብለዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ የግዙፍ ፕሮጀክቶች ሥራ

አለመቆሙን ለእንደራሴዎቹ የነገሯቸው ጠቅላዩ፣ ከአፍሪካ አንደኛው የኤርፖርት ግንባታም ተጀምሯል ብለዋል።

ከሕዳሴው ግድብ በመለስ፣ የኤርትራን ጉዳይም ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፣ እስከዛሬ ከመንግስታቸው በይፋ ያልተነገሩ ጉዳዮችን በዚኹ የዕለተ ማክሰኞች ውሏቸው ሲያነሱ ተሰተውለዋል። በዚኽም፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ወቅት በኤትርትራ ወታደሮች ተፈጸሙ ስላሏቸው ውድመቶች የዘረዘሩት ጠቅላይ ጦር አዛዡ፣ በኤርትራ እና በኢትዮጵያ መካከል አለመግባባት የጀመረው ኢትዮጵያ ቀይ ባሕር ጉዳይን ስታነሳ ነው የሚሉ ወገኖች መኖራቸውን በማንሳትም፣ ይህ ስህተት መሆኑን ተናግረዋል።

በኹለቱ አገራት መካከል አለመግባባት የተጀመረው በሰሜኑ ጦርነት ወቅት መሆኑን የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የተለያዩ ጥፋቶች በኤርትራ ወታደሮች መፈጸማችን ተናግረዋል። “ኤርትራ ከተፈጠረች ጊዜ ጀምሮ በኤርትራ እና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ችግር ነበረ፤ እኛ ከመጣን በኋላ አያስፈልገንም ይቅርብን ብለን ለምነናል" ሲሉም ለእንደራሴዎቹ ተናግረዋል። “ፀቡ የተጀመረው ብዙዎች እንደሚያስቡት የቀይ ባሕር ጉዳይ ሲመጣ አይደለም" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ “በትግራይ ውጊያ ሲጀመር በመጀመሪያው ዙር ወጊያ ሽሬን ካስለቀቅን በኋላ የኤርትራ ጦር ከኋላ የአንዳንድ ግለሰቦችን ቤት፣ ፎቅ ማፍረስ ሲጀምር ፀብ ተጀምሯል፤ አልተናገርንም እንጂ” ሲሉም፣ የጸቡን መነሾ ያሉትን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጠቅሱ ተሰምተዋል።

“አክሱምን ይዘን ስናልፍ፣ አክሱም ገብቶ ወጣቶችን በጅምላ ሲረሽን ፀብ ተፋፍሟል፤ አድዋን ይዘን ስናልፍ፣ አድዋ ሄዶ ፋብሪካዎችን ሲፈታታ፣ ሲሰርቅ ፀብ ተጋግሏል” ያሉት ጠቅላዩ፣ “አዲግራት ደርሰን የመድኃኒት ፋብሪካውን የሚነቀለውን ነቅሎ የማይነቀለውን ሲያፈራርስ ፀቡ ጫፍ ደርሷል፤ ግን ያኔ የኢትዮጵያ መንግስት በዚኽም በዚያም ለመዋጋት አቅም አልነበረውም” ብለዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይኽንን ጉዳይ በተመለከተ ከኤርትራ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጋር እንዲነጋገሩ የቀድሞውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ገዱ አንዳርጋቸውን እንዲኹም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩትን ደመቀ መኮንንን ወደ ኤርትራ መላካቸውን ጭምርም ተናግረዋል። ይሄ ጸብ ተፋፍሞ ሄዶ የፕሪቶሪያ ስምምነት ሲፈረም፣ “እንዴት ሕወሓት ሳይጠፋ፣ ትግራይ ሳይወድም ፊርማ ይደረጋል በሚል ነው ፀቡ ጫፍ የደረሰው" ሲሉም የጸቡ መነሾ ያሉትን ሂደት ለእንደራሴዎቹ አብራርተውላቸዋል።

ከኤርትራ ተኮሩ ማብራሪያቸው ለጥቀው ወደ ሰንባቹ የባሕር በር ጉዳይ የተሻገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በቀደሙት የምክር ቤት ውሏቸው ያነሷቸውን የመንግስታቸውን አቋሞች በድጋሚ አጽንዖት ሰጥተው ተናግረዋል። የአፍሪካ ቀንድ እንዳይቀደድ የተሰፋ፣ እንዳይጣመር የተቀፈደደ አካባቢ ነው ሲሉ የተሰሙት ዶ.ር. ዐቢይ፣ እንዳንለያይ አንድ ዓይነት ዘር፣ቋንቋ፣ ባህል አለን፤ እንዳንጣመር እና አብረን እንዳንሰራ ደግሞ ብዙዎቻችን ብሔራዊ ጥቅማችን ላይ አይደለም እየሰራን ያለነው ሲሉም፣ ከፍተኛ ጣልቃ ገብነት እና ከፍተኛ ፉክክር ያለበት አከባቢ ስለመሆኑ ጠቅሰዋል።

“ቀይ ባሕር እና ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ተነጣጥለው መኖር አይችሉም” ያሉት የተከበሩ ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት እና ሕዝብ ቀይ ባሕርን ለመጠቀም ሰው ልግደል አላለም፤ በውውይት እና በስምምነት እንዲኹም በገበያ ሕግ እና በድርድር ጉዳዩን እንፍታው ነው

ያልነው ብለዋል። እኛም ማጋራት አለብን፤ እነሱም ማገዝ አለባቸው፤ ኢትዮጵያን ጎድቶ ትርፋማ መሆን አይቻልምም ሲሉ ተናግረዋል። ኢትዮጵያ የባሕር በር አያስፈልጋትም ብሎ የሚያስብ ሰው አንድ ተፈጥሯዊ ሕግ የሳተ ነው ያሉት ርዕሰ-መንግስቱ፣ የኢትዮጵያን የባሕር በር ጥያቄ በተመለከተም በዲፕሎማሲ እና በሰጥቶ መቀበል ለማሳካት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፣ ሆኖም “በባሌም ሆነ በቦሌ እንደተባለው ግን አይቀርም ማለት ነው” ሲሉ አክለዋል።

## 3. የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት

እንደራሴዎቹ፣ በወርኃ ጥር ኢትዮጵያ ከተለያዩ አገራት ጋር ስምምነት ላይ የደረሰችባቸውን ወንጀል ነክ ዐዋጆችን ሲያጸድቁ፤ አራት ረቂቅ ዐዋጆችን ደግሞ ይመለከታቸዋል ላሏቸው ቋሚ ኮሚቴዎች መርተዋቸዋል። ከዚያ ባለፈም ኹለት አስረጂ መድረኮችን ከውነዋል።

### 3.1 የጸደቁ ሕግጋት

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወርኃ ጥር፣ **በኢትዮጵያ እና በተለያዩ አገራት መካከል ፍርደኞችን ማስተላለፍ እንዲኹም የወንጀል ጉዳይን የአሳልፎ መስጠት የሚያስችሉ ዐዋጆችን አጽድቋል።** ምክር ቤቱ ባካሄደው 9ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ ፍርደኞችን የማስተላለፍ ስምምነቱ በኢትዮጵያ እና በሕዝባዊት ሪፐብሊክ ቻይና እንዲኹም በኢትዮጵያ እና በብራዚል ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገ መሆኑን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎችን የአሳልፎ የመስጠት ስምምነቱ ደግሞ በኢትዮጵያ እና በደቡብ አፍሪካ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገ ነው ተብሏል፡፡ ረቂቅ ዐዋጆቹን አስመልክቶ በምክር ቤቱ የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተዘጋጀውን የውሳኔ ሀሳብ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ እጸገነት መንግስቱ አቅርበዋል፡፡ ሰብሳቢዋም፣ በተለያዩ ወንጀሎች ምክንያት ዜጎቻቸው ተፈርደባቸው ፍርዳቸውን በአገራቸው ጨርሰው ወደ ማኅበረሰባቸው እንዲቀላቀሉ በማድረግ የመታረም ሂደቱን ውጤታማነት የሚያግዝ ዐዋጅ መሆኑን መናገራቸው ተጠቅሷል።

ስምምነቶቹ ፍርደኞቹ ከሚያውቁት ማኅበረሰብ፣ ቋንቋ እና ባህል ጋር በቅርበት ፍርዱን እንዲፈጽሙ እና ፍርዳቸውን በአገራቸው እንዲጨርሱ ይረዳል ያሉት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ፣ በኢትዮጵያ እና በእነዚኽ አገራት መካከል የተደረጉት ስምምነቶች የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሂደትን ያገናዘቡ፣ ዓለም አቀፍ አሰራርን መሰረት ያደረጉ ውጤታማ የሆነ የወንጀል መከላከል ትብብር ማድረግ፣ የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ እና የፍትሕ ሥርዓትን ለማስፈን ጠቀሜታቸው የጎላ እንደሆነም መናገራቸውን መረጃው ጠቅሷቸዋል። በተለይ ኢትዮጵያ እና ቻይና እንዲኹም ኢትዮጵያ እና ደቡብ አፍሪካ በንግድ እና የመዋዕለ-ንዋይ ዘርፍ ያላቸው ግንኙነት እየጨመረ በመሆኑ፣ ተጠርጣሪዎች እና ወንጀለኞች ይኽንን ኹኔታ በመጠቀም ከሕግ ለማምለጥ ወደ ኹለቱም አገራት ለመሄድ የሚችሉበትን አጋጣሚ ሰፊ እንደሚያደርገው በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተገልጿል ተብሏል፡፡ እንደራሴዎቹም ዐዋጆችን በሙሉ ድምጽ አጽድቀዋቸዋል።



*በምክር ቤቱ የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተዘጋጀውን የውሳኔ ሐሳብ ሰብሳቢዋ የተከበሩ ወ/ሮ እጸገነት መንግስቱ ባቀረቡበት ወቅት፤*

## 3.2 ረቂቅ ሕግጋት

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በወርኃ ጥር አጋማሽ ባደረጉት 9ኛ መደበኛ ስብሰባ ሦሥት ረቂቅ ዐዋጆችን ይመለከታቸዋል ላሏቸው የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች መርተዋል። አንደኛው፣ **የኅብረት ሥራ ማኅበራት ረቂቅ ዐዋጅ** ሲሆን፣ ረቂቁን አስመልክቶም በምክር ቤቱ የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታዋ የተከበሩ ወ/ሮ መሰረት ኃይሌ ረቂቅ ዐዋጁ፣ ዘመናዊ፣ ተወዳዳሪ እና ውጤታማ ለማድረግ የግብይት ሥርዓቱን ለማዘመን እና በዘርፉ የኢኮኖሚ ድርሻን ለማሳደግ የነባሩ ዐዋጅ መሻሻል አስፈለገ ሆኖ መገኘቱን አስረድተዋል ተብሏል። ምክር ቤቱም ረቂቅ ዐዋጁን፣ ዐዋጅ ቁጥር 6/2018 አድርጎ ለዝርዝር ዕይታ ለግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሙሉ ድምጽ መርቶታል፡፡

ኹለተኛው ረቂቅ ዐዋጅ፣ **የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኩዩሪቲ ዐዋጅን** ለማሻሻል የቀረበ ረቂቅ ሲሆን፤ ይኽንኑ ረቂቅ ዐዋጅንም ለእንደራሴዎቹ ያብራሩት የተከበሩ ወ/ሮ መሰረት ኃይሌ ነበሩ። ወ/ሮ መሰረት በሰጡት ይኽው ማብራሪያ፣ ወቅቱን የሚመጥን እና የአገር ደኅንነትን የሚጠበቅ የአቪዬሽን ሥርዓት እንዲኖር ለማስቻል እና ዘርፉን በቴክኖሎጂ ለማዘመን እንዲያግዝ ነባሩን ዐዋጅ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን አስረድተዋል፡፡

ዓለም አቀፍ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት የአየር ትራንስፖርት ደኅንነት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ እንዲጠበቅ ለማድረግ ወቅታዊ የአየር ደኅንነት ስጋቶችን ለመከላከል ረቂቅ ዐዋጁ እንደሚያግዝም የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢዋ መግለጻቸው ተዘግቧል። ምክር ቤቱም ዓለም አቀፍ የሲቪል ረቂቅ ዐዋጁን፣ ለውጭ ግንኙነት እና ሰላም ጉዳዮች እና በተባባሪነት ለከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴዎች ለዝርዝር ዕይታ በሙሉ ድምጽ መርቶታል፡፡

ሦሥተኛው የወሩ ረቂቀ ዐዋጅ፣ **የፌዴራል የስፖርት ልማት እና አሥተዳደር** የተሰኘው ሲሆን፤ በዚኽ ረቂቅ ዐዋጅ ዙሪያም ለእንደራሴዎቹ ማብራሪያ የሰጡት፣ እንደቀደሙት ረቂቆች ኹሉ የተከበሩ ወ/ሮ መሰረት ሲሆኑ፤ እርሳቸውም፣ የስፖርት ዘርፍ ካለው ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እንዲኹም አሥተዳደራዊ ውስብስብነት አንፃር በአግባቡ ለመምራት እና ለመቆጣጠር እንደሚያስፈልግ እና በርካታ ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ የሕግ ማዕቀፍ እና አሥተዳደራዊ የአሰራር ሥርዓት ለመዘርጋት ረቂቅ ዐዋጁ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው አስረድተዋል ተብሏል።

ምክር ቤቱም፣ ረቂቅ ዐዋጁን መርምሮ ለዝርዝር ዕይታ ለጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መምራቱ ተዘግቧል።

በወሩ ምክር ቤቱ የተመለከተው ሌላይኛው ረቂቅ ዐዋጅ፣ **የብድር ስምምነትን** የተመለከተው ነበር። የጤና ተቋማትን አገልግሎት እና ተደራሽነትን ለማሻሻል የሚያግዝ የተባለውን የብድር ስምምነት አስመልክቶ ለእንድራሴዎቹ ማብራሪያ የሰጡት በምክር ቤቱ የመንግስት ተጠሪዋ ወ/ሮ መሰረት፣ የብድር ስምምነቱ የኢትዮጵያ መንግስት የጤና አገልግሎቱን ጥራት እና ተደራሽነት ለማረጋገጥ የተለያዩ ስትራቴጂካዊ ተግባራትን ለማከናወን እንደሚያግዝ ተናግረዋል ተብሏል።

የጤና አገልግሎት ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ በመምጣቱ አዳዲስ የጤና ተቋማትን በህክምና መሳሪያዎች ማደራጀት ቀዳሚ ተግባር መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፣ ይሁን እንጂ፣ የህክምና መሳሪዎች

ወጪ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚጠይቅ በመሆኑ፣ የመለዋወጫ እቃዎች እጥረት እና የጥገና ባለሙያዎች አቅም ውስንነት በዘርፉ ላይ ተግዳሮት ሆኖ መቆየቱን አብራርተዋል፡፡ ምክር ቤቱም፣ ረቂቅ ዐዋጁን ለዝርዝር ዕይታ በምክር ቤቱ ለፕላን፣ በጀት እና እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሙሉ ድምጽ መርቶታል ተብሏል።



*በምክር ቤቱ የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታዋ የተከበሩ ወ/ሮ መሰረት ኃይሌ፣ ረቂቅ ዐዋጆቹን ሲያብራሩ፤*

## 3.3 አስረጂ መድረኮች

በወሩ የተካሄደው አንዱ አስረጂ መድረክ፣ **የኢትዮጵያ የአቭዬሽን ደኅንነት ዐዋጅ** ቁጥር 432/1997ን ለማሻሻል በቀረበው ረቂቀ ዐዋጅ ዙሪያ እንደነበር የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል። የአስረጂ መድረኩን የመራው፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፣ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎም፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ ተቀባይነትን ያተረፈ ተቋም መሆኑን ገልፀው፣ ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጁ የአየር መንገዱን ተቀባይነት ለማስቀጠል ወቅቱን የዋጁ እና ለረጅም ጊዜ የሚያገለግሉ አገራዊ እና ዓለም ዓቀፍ የአቭዬሽን ደኅንነት የሕግ ማዕቀፎች መቃኘት እንዳለበት አመላክተዋል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ፈቲሕ ማህዲ በበኩላቸው፣ ዐዋጁ በሚወጣበት ወቅት አየር መንገዱ የዓለም ዓቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ያስቀመጣቸውን የሕግ ድንጋጌዎች በማሟላት እና የመንገደኞችን ደኅንነት በተሻለ ደረጃ ለመጠበቅ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ተነግረዋል።



*የብሔራዊ መረጃ እና ደኅንነት አገልግሎት ምክትል ጄነራል ዳይሬክተር አቶ እርስቱ ይርዳው*

የብሔራዊ መረጃ እና ደኅንነት አገልግሎት ምክትል ጄነራል ዳይሬክተር አቶ እርስቱ ይርዳው በተራቸው፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዓመት ከ20 ሚሊዮን በላይ ተጓዦችን እንደሚያስተናግድ ገልጸው፣ የእነዚኽን ደንበኞች ደኅንነት ለማረጋገጥ እና የደኅንነት ጉዳይ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ኹኔታውን እየተቀያየረ እና ውስብስብ እየሆነ በመምጣቱ ዐዋጁን ማሻሻል እንዳስፈለገ መግለጻቸው ተጠቅሷል። ዳይሪክተሩ አክለውም፣ ረቂቅ ዐዋጁ በአቭዬሽን ደኅንነት ዘርፍ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተደንግገው እየተሰራባቸው የሚገኙ የሕግ ማዕቀፎች በአገራችን በሕግ እንዲደገፉ እንደሚያስችልም አክለው ሲናገሩ ተደምጠዋል።

በወርኃ ጥር የተካሄደው ኹለተኛው አስረጂ መድረክ፣ **ኢትዮጵያ ከደቡብ ኮሪያ ሪፐብሊክ ጋር** የተስማማችውን አንድ የብድር ስምምነት ረቂቅ ዐዋጅ አስመልክቶ የተደረገ መሆኑን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። በዚኹ ረቂቅ ዐዋጅ ዙሪያ፣ በምክር ቤቱ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር የአስረጂ መድረኩን አካሂዷል።

በመድረኩም የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ፣ የአገሪቱ የብድር ስምምነት በሕገ-መንግሥቱ መሠረት ገንዘብ ሚኒስቴር ከአገሪቱ ኢኮኖሚ ጥቅም አኳያ የውጭ ብድር ስምምነት እንዲከናወን ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን ገልጸው፣ የቀረበው የብድር ስምምነት አስፈላጊ እንደሆነም ተናግረዋል ተብሏል። በአገሪቱ የተለያዩ ሆስፒታሎች ቢገነቡም በቂ የህክምና መሳሪያ ባለመኖሩ ይኽ የብድር ስምምነት በጤናው ዘርፍ ያለውን የህክምና መሳሪያዎች እጥረት የሚያቃልል መሆኑንም ሰብሳቢው አክለው ጠቅሰዋል።



***የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትሩ የተከበሩ አሕመድ ሺዴ፣ በአስረጂ መድረኩ ላይ፤***

የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትሩ የተከበሩ አሕመድ ሺዴ በበኩላቸው፣ ይኽ የብድር ስምምነት በመላው አገሪቱ የሚገኙ የጤና ተቋማትን የጤና አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዝ በመሆኑ፣ የህክምና መሳሪያዎችን ለማሟላት እንዲኹም ስለመሳሪያዎቹ አያያዝ እና አጠቃቀም ለጤና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና የሚውል መሆኑን አብራርተዋል፡፡ ከዚያ ባለፈም ሚኒስትሩ፣ ባለፉት ሰባት ዓመታት መንግስት ከፍተኛ የሆነ የዐብይ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በማድረግ በርካታ ተግባራት መከናወናቸውን ገልፀው፣ የቀረበው የብድር ስምምነት ወቅታዊ እና ተገቢ መሆኑን አንስተዋልም ብሏል።

## 4. የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በዚኹ ወር የአምስት ተቋማትን የበጀት ዓመቱን የስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች በኩል ሲገመግም፣ የአንድ የፌደራል ተቋምን አኹነኛ ሪፖርትም አድምጧል።

### 4.1 የተቋማት ሪፖርቶች

የወሩ ቀዳሚ የስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት አቅራቢ የነበረው **የከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር** ሲሆን፣ የተቋሙን ሪፖርትም ያደመጠው በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ፕ/ር መሃመድ አብዶም፣ የቤት ችግርን ሙሉ በሙሉ መፍታት ባይቻልም በሌሎች አገራትም ችግሩን ለመፍታት ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች አንዱ የቤት ብድር ባንክ አገልግሎት መሆኑን በመጥቀስ፣ መንግስት አዲስ ከማዋቀር ይልቅ የነበረውን የኮንስትራክሽን ባንክ መልሶ ማደራጀት እንዳለበት ተናግረዋል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ/ር እሸቱ ተመስገን በበኩላቸው፣ በኢትዮጵያ ቀደም ባሉት ዘመናት የቤት ብድር ባንክ እንደነበረና ባልታወቀ ምክንያት ወደ ንግድ ባንክ የተቀላቀለ መሆኑን አንስተው፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ኃላፊነቱን ወስዶ ይኽንን ባንክ መልሶ እንዲደራጅ በትኩረት መሥራት እንደሚገባው አሳስበዋል። የከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ወ/ሮ ጫልቱ ሣኒ የቤት ልማት ፋይናንስ ችግርን ለመፍታት የቤት ብድር የባንክ ሥርዓት እንዲዘረጋ የእንደራሴዎቹ እና የቋሚ ኮሚቴው ድጋፍ ያስፈልጋል ማለታቸው ተጠቅሷል።



*የከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ፕ/ር መሃመድ አብዶ፣ በሪፖርቱ ወቅት፤*

**የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ** የተሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ እየተወጣ መሆኑ የተገለጸበት ደግሞ፣ ኹለተኛው የወሩ የሥራ አፈጻጸም የእንደራሴዎቹ ክንውን ነበር። የተቋሙን የዚኽ በጀት ዓመት የስድስት ወራት እቅድ የገመገመው በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፣ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መናም፣ ባንኩ ከመደበኛ የባንክ ሥራው ጎን ለጎን ማኅበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት 67.8 ሚሊዮን ብር መድቦ የልማት ክፍተት ባለባቸው የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሠራው ሥራ የሚበረታታ መሆኑን ገልፀዋል ተብሏል። ሰብሳቢው አያይዘውም ባንኩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣውን የሕዝብ ፍላጎትን ታሳቢ ያደረገ አገልግሎቶቹን በማስፋት ትርፍን ከደንበኞች እርካታ ጋር በማጣጣም ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይኖርበታል ብለዋል።

የቋሚ ኮሚቴው አባላት በበኩላቸው፣ ባንኩ ከተደራሽነት እና ከብድር አቅርቦት አንጻር ያለበትን ክፍተት በመሙላት

ፈጣን እና ቀልጣፋ አገልግሎት ለዜጎች ለመስጠት በትኩረት መሰራት እንዳለበት አስገንዝበዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ምክትል ፕሬዝዳንት አቶ ኤፍሬም መኩሪያ በበኩላቸው፣ ባንኩ በግማሽ ዓመቱ በዲጂታል ባንኪንግ እና በትርፋማነት እንዲኹም ከሀዋላ የሚያገኘውን ገቢ ለማሳደግ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን መጥቀሳቸው ተጠቅሷል፤ አክለውም ባንኩ የሲቢኢ እና የሞባይል ባንኪንግ ተጠቃሚዎችን ቁጥር በማሣደግ የዲጂታል ኢኮኖሚውን ለመምራት እየሰራ መሆኑን አብራርተዋል።



*የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ምክትል ፕሬዝዳንት ኤፍሬም መኩሪያ ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ፤*

ወደ እንደራሴዎቹ ምክር ቤት ብቅ ያሉት **የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ** ገዢው ዶ.ር. ኢዮብ ተካልኝ የተቋማቸውን የዚኽን በጀት ዓመት የስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያቀረቡበት መድረክም፣ እንዲ የዚኹ ወር የእንደራሴዎቹ የሥራ አሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር ክንውን ነበር።

የባንኩን የመንፈቅ ዓመት ሪፖርት ያደመጠው፣ በምክር ቤቱ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፣ ኮሚቴውም ባንኩ ባለፉት ዓመታት ባደረጋቸው ዘርፈ ብዙ የፖሊሲ እና የመመሪያ የለውጥ ሥራዎች አበረታች ውጤቶች ማስመዝገቡን መጠቀሱ ተዘግቧል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጆም፣ ከ17 በመቶ በላይ የነበረው የዋጋ ንረት በ2018 ዓ.ም. 6 ወራት ውስጥ ወደ 9.7 በመቶ ማውረድ መቻሉ አበረታች መሆኑን ገልጸዋል። የተገኘውን ውጤት ዘላቂ ማድረግ እና የማኅበረሰቡን የኑሮ ጫና ለመቀነስ አሁንም በትኩረት መሥራት እንደሚገባ ጨምረው የጠቀሱት ሰብሳቢው፣ በ6 ወራት ውስጥ 5 ቢሊየን ዶላር መገኘቱ ከባለፈው ዓመት የ13 በመቶ ጭማሪ እንደመሆኑ፣ ይኽም የተካሄዱት የለውጥ ሥራዎች ውጤት መሆኑንም ተናግረዋል ተብሏል።

ከፍተኛ ገቢ ከተገኘባቸው ከቡና እና ከወርቅ በተጨማሪ ሌሎች ምርቶች ላይ መሥራት አስፈላጊ መሆኑን ያነሱት የተከበሩ ደሳለኝ የብድር ተደራሽነትን ለማሳደግ በተለይ በተንቀሳቃሽ ንብረቶች የሚሰጥ ብድርን በማሳደግ ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባልም ብለዋል ተብሏል።

የብሔራዊ ባንክ ገዢው ዶ.ር. ኢዮብ ተካልኝ በበኩላቸው፣ ባለፉት ዓመታት በፋይናንስ ዘርፍ የተከናወኑ የለውጥ ሥራዎች የተሳካ ውጤት ማምጣታቸውን ተናግረዋል። ባለፉት 6 ወራት ለባንኮች የቀረበው የብድር አገልግሎት ከ600 ቢሊየን ብር በላይ መሆኑን በሪፖርታቸው የጠቀሱት ዶ.ር. ኢዮብ፣ ባንኮች ከ4 ነጥብ 2 ትሪሊዮን ብር በላይ በማንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኙም አመላክተዋል።

የኑሮ ውድነትን በመቀነስ፣ የውጪ ምንዛሬ ግኙትን በማሳደግ እና የብድር አቅርቦትን በመጨመር ዙሪያ የተመዘገቡትን ውጤቶች ለማስቀጠል በቀጣይ በትኩረት እንሰራለን ሲሉም ለቋሚ ኮሚቴው አባላት ነግረዋቸዋል።



*የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥው ዶ.ር. ኢዮብ ተካልኝ የተቋማቸውን የስድስት ወራት ሪፖርት ሲያቀርቡ፤*

የወርኃ ጥር ዐራተኛ ተረኛ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት አቅራቢ የነበረው **የኢትዮጵያ ባሕር ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ አገልግሎት** ሲሆን፣ የዚኽን ተቋም የበጀት ዓመቱን የስድስት ወራት የሥር አፈጻጸም ያደመጠው ደግሞ በምክር ቤቱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መናም፣ ተቋሙ የአገሪቱን ዕድገት ታሳቢ ያደረጉ ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ ገልጸው፣ በተለይም የፋይናንስ ሥርዓቱ ጤናማ መሆኑ እና የውጭ ምንዛሪ ግኝት አፈጻጸሙም ለሌሎች የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአርአያነት የሚጠቀስ ነው ብለዋል። የድርጅቱ ኦፕሬሽን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን እና በባሕር እና በየብስ ትራንስፖርት የሚጓጓዙ ንብረቶች 99 በመቶ ያለምንም ብልሽት መድረሳቸው የሚበረታታ መሆኑን ሰብሳቢው አክለውም ጠቁመዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ስለሺ ኮሬ በበኩላቸው፣ በገቢ አፈጻጸም ረገድ የታየው ስኬት የሚበረታታ ቢሆንም ተቋሙ በዘርፉ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቀጠል ጥራትን እና ጊዜን መሠረት ያደረጉ ልኬቶችን ጠብቆ መሥራት እንደሚገባው ተናግረዋል ተብሏል። የኢትዮጵያ ባሕር ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ዋና ሥራ አሥፈጻሚ ኢንጂነር አብዱልበር ሽምሱ ለቋሚ ኮሚቴው ባቀረቡት ሪፖርት፣ በግማሽ በጀት ዓመቱ 65.5 ቢሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዶ 74.43 ቢሊዮን ብር መገኘቱን ጠቅሰው፣ ይኽም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ59 በመቶ ዕድገት ማሳየቱን መግለጻቸው ተዘግቧል። ኢንጂነሩ በዚኹ ሪፖርታቸው፣ በጅቡቲ ወደብ በኩል ወደ አገር ውስጥ ከገባው 4.7 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን በላይ የደረቅ ጭነት ውስጥ ድርጅቱ 40 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ በመሸፈን ሲያጓጉዝ፣ በተለይም የአፈር ማዳበሪያ ማጓጓዝ ሥራው ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር የ191 በመቶ ዕድገት ማሳየቱን አብራርተዋል።



*የመንግስት የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት የተቋሙን ሪፖርት ሲያደምጡ፤*

በዚኹ ጥር ወር የመጨረሻ ሳምንት ላይ፣ ከላይ እንደተጠቀሱት ተቋማት ኹሉ የበጀት ዓመቱን የስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸሙን ለማቅረብ የተጠራው **የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን** ሲሆን፤ የተቋሙን ሪፖርት ያደመጠው ደግሞ በምክር ቤቱ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር።

የቋሚ ኮሚቴው ስብሳቢ የተከበሩ መለስ መናም፣ ከአቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ውይይቱ በኋላ በሰጡት ማጠቃለያ አስተያየት፣ ኮርፖሬሽኑ የተጣለበትን አገራዊ አደራ በብቃት መወጣት የሚያስችለው አሰራር መከተሉ እና ከገቢ አሰባሰብ አንፃር ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በእጥፍ ያደገ መሆኑን በጥንካሬ አንስተው ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ብለዋል ተብሏል። ሰብሳቢው አክለውም፣ የተቋሙ ቅንጅታዊ አሰራር፣ የተበላሹ አሰራሮችን ከማስተካከል እና ከኦዲት ግኝት ነፃ ለመሆን የሄዱበትን ርቀት በጥንካሬ አንስተው፣ እነዚኽ መልካም አፈፃፀሞች ወደኋላ እንዳይመለሱ ትኩረት መስጠት ይገባል ሲሉም አስገንዝበዋል።

የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አሥፈፃሚ ዶ.ር. ረሺድ ከማል በበኩላቸው፣ በተቋም ግንባታ ረገድ የተከናወኑ ተግባራትን፣ የዜጎችን የቤት ጥያቄ ለመመለስ እና የተቋሙን የገቢ አቅም ለማሳደግ እንዲኹም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለማዘመን እና ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ የተሰሩ ሥራዎችን ለቋሚ ኮሚቴው አስረድተዋል። በቋሚ ኮሚቴው ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል ተብለው የተነሱ ነጥቦችንም እንደ ግብአት ወስደው፣ የተጣለባቸውን አገራዊ ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት በትኩረት የሚሰሩ መሆኑንም ዋና ሥራ አሥፈፃሚው መግለጻቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል።



*የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ መለስ መና፤*

ከእዚኽ መሰሎቹ የዓመት ከመንፈቅ ተቋማዊ ሪፖርቶች ባለፈ፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ አንድ ተቀራራቢ ኹነትም ከውኖ ነበር። ለዚኹ ቋሚ ኮሚቴ ሪፖርቱን ያቀረበው **የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን** ሲሆን፤ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዕውነቱ አለነ፣ አገራዊ ምክክሩ ለአገሪቱ የመጣ ወርቃማ ዕድል በመሆኑ ለውጤታማነቱ ኹሉም ዜጋ ሊረባረብ እንደሚገባ ገልጸዋል ተብሏል።

ኮሚሽኑም፣ የአጀንዳ ልየታ ሥራ ማከናወኑን አስመልክቶ ለቋሚ ኮሚቴው ሪፖርት ማቅረቡ ሲጠቀስ፤ በዕለቱም፣ ልዩነቶችን በኀይል ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ ወርቃማ ዕድል ወደሆነው አገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ማምጣቱ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ሰብሳቢው አስገንዝበዋል ተብሏል።

ኮሚሽኑ በበርካታ የአገሪቱ ክፍሎች በመዘዋወር የአጀንዳ ልየታ ሲያከናውን መቆየቱን እና የእስካኹኑ ሂደት ስኬታማ መሆኑንም ገልጧል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ አዝመራ አንዴሞ በበኩላቸው፣ የአሠራር ሥርዓትን ለመገንባት እና ለትውልድ ለማሸጋገር በዲጅታል ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራት የሚበረታቱ እና ለሌሎችም በተሞክሮነት የሚወሰዱ መሆኑን አስገንዝበዋል።

የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያም፣ ተግባራቶችን ለትውልድ ተሻጋሪ ለማድረግ የዲጂታል አሰራርን መሠረት በማድረግ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን መናገራቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል። የቋሚ ኮሚቴው አባላት በበኩላቸው፣ የተከናወኑ ተግባራት ስኬታማ እንደነበሩ ገልጸው፣ ቀሪ ሥራዎችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ኹሉም የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ማሳሰባቸውም ተነግሯል።



*የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነሩ ፕ/ር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ፤*


## 4.2 የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች

በዚኽኛ የአንደራሴ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወር፣ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ከዐሥር ያላነሱ ተቋማት በወካዮቻቸው በኩል በአካል ሲጎበኙ፤ ከአምስት ወዳለነሱ ክልሎችም ይመለከታቸዋል ያሏቸውን የቋሚ ኮሚቴ አባላት ወክለው የመስክ ምልከታዎች ከውነዋል።

### 4.2.1 የተቋማቱ ጉብኝቶች

እንደራሴዎቹ፣ በዚኹ ወር ሊጎበኟቸው ከወሰኑት ተቋማት መካከል በጊዜ ምጣኔ ቀዳሚ ማሳያ የሚሆነው በኢፌድሪ መከላከያ ስር የሚገኘው **የምሥራቅ ዕዝ** ሲሆን፣ ወታደራዊ ተቋሙን የጎበኘውም፣ በምክር ቤቱ የውጪ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ ዕዙ የአገርን ዳር ድንበር በማስከበር እና ሰላምን በማስፈን የተጣለበትን አገራዊ ተልዕኮ በላቀ ደረጃ በመወጣት ውጤታማ ተግባራትን አጠናክሮ እንዲቀጥል አሳስበዋል።



*የውጪ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የምስራቅ ዕዝን የሥራ እንቅስቃሴዎችን ተዘዋውሮ በተመለከተበት ወቅት*

ሰብሳቢው አክለውም፣ ዕዙ ከተጣለበት ኃላፊነት በተጨማሪ በተለያዩ የልማት ሥራዎች የአካባቢውን እና የሠራዊቱን ኑሮ ለማሻሻል እያከናወነ ያለው ተግባር ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ገልጸዋል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማህዲ በበኩላቸው፣ ዕዙ እያከናወናቸው ባሉት የማሻሻያ ሥራዎች የተመዘገቡት ውጤቶች በተሞክሮነት የሚወሰዱ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

የምሥራቅ ዕዝ ምክትል አዛዥ ሜጄር ጄኔራል ፍቃዱ ፀጋዬ በበኩላቸው፣ ዕዙ የአገርን ድንበር በመጠበቅ፣ የአሸባሪ ቡድኖች እንቅስቃሴን በመግታት እና የኮንትሮባንድ ንግድን በመከላከል ግዳጁን በመወጣት ላይ እንደሚኝ ገልጸዋል ተብሏል።

እንደራሴዎቹ፣ በዚኹ ወር የከፍተኛ ደረጃ የትምህርት ተቋምን ጎብኝተው እንደነበርም ከምክር ቤቱ የተገኘው

መረጃ ይጠቁማል። ማሳያ የሚሆነውም **አምቦ ዩንቨርሲቲ** ሲሆን፣ ዩንቨርሲቲውን የጎበኘው በምክር ቤቱ የሰው ኃብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፣ ቋሚ ኮሚቴው የዩኒቨርሲቲውን የ2018 ዓ.ም. የመማር ማስተማር እንቅስቃሴ በመመልከት የተማሪዎች የመውጫ ፈተና የማለፍ ምጣኔን ለማሳደግ መሥራት እንደሚገባው ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ መግለጻቸው ተዘግቧል። ሰብሳቢው አክለውም፣ በዩኒቨርስቲው በሚሰሩ የጥናት እና የምርምር ሥራዎች ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚደረጉ ጥረቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉም አሳስበዋል ተብሏል። የዩንቨርሲቲው ፕሬዝደንት ዶ.ር. ባይሳ ለታ በበኩላቸው፣ ዩኒቨርሲቲው የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ እና መልካም አሥተዳደርን ለማስፈን እየሰራ እንደሚገኝ የዩኒቨርስቲው ተናግረዋል ሲል ዘገባው ጠቅሷቸዋል።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ በኢትዮጵያ ግብርናን የማዘመኑ ሥራ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ያሳሰበት፣ **የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን** የተቋም ምልከታ ደግሞ ሌላይኛው የወሩ ማሳያ ጉብኝት ነበር።

የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አሥፈፃሚ ወ/ሮ የሺመቤት ነጋሽ፣ የተቋሙን አፈጻጸም በሚመለከት ለቋሚ ኮሚቴው አባላት ሪፖርት ያቀረቡ ሲሆን፣ የኮርፖሬሽኑን አጠቃላይ ነባራዊ ኹኔታ በመገምገም ተቋሙ በቀጣይ በገበያ ውስጥ ብቁ ተወዳዳሪ፣ ምርታማ እና አትራፊ ሆኖ እንዲቀጥል የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሰሩ ስለመሆኑ ማስረዳታቸውን መረጃው ጠቅሷል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና፣ የኮርፖሬሽኑ አዲሱ አመራር የተቋሙን አጠቃላይ ኹኔታ በአጭር ጊዜ በመረዳት ተቋሙ በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ፣ ምርታማ እና አትራፊ ሆኖ እንዲቀጥል እያደረገ ያለውን ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል አሳስበዋል ተብሏል፡፡ በዚኽ አስተያየታቸው ብቻ ያላበቁት ሰብሳቢው፣ ኮርፖሬሽኑ በጥናት ላይ የተመሠረተ እና በቴክኖሎጂ የታገዘ የግዥ እና ሽያጭ አሠራር መዘርጋት እንዳለበት እና የማዳበሪያ፣ ትራክተር፣ ኮምባይነር እና ሌሎች የግብርና ግብዓቶችን በጊዜ እና በጥራት ለተጠቃሚዎች ማቅረብ እንደሚገባም ሰብሳቢው አጽንዖት ሰጥተው መናገራቸውን ዘገባው ጠቅሷቸዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ስለሺ ኮሬ በበኩላቸው፣ ኮርፖሬሽኑ ለግብርና ትራንስፎርሜሽን ወሳኝ ተቋም መሆኑን ገልጸው፣ ትርፋማነትን እና ሕዝብን የማገልገል ተልዕኮውን በብቃት ሊወጣ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

በኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ካሉት ቋሚ ኮሚቴዎች መካከል ከላይ የተጠቀሰው የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ተቆጣጣሪው ቋሚ ኮሚቴ፣ በዚኽ ጥር ወር ከሌሎቹ ቋሚ ኮሚቴዎች በዛ ያሉ የተቋማት ጉብኝቶችን ማድረጉን ከምክር ቤቱ የተሰባሰቡት መረጃዎች ያመለክታሉ። በተለይም፣ **በኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ ሥር የሚገኙትን ግዙፍ የስኳር ፋብሪካዎች** መጎብኘቱ ሊጠቀስ የሚችል ነው። በኦሞ ኩራዝ ስኳር ፋብሪካ የመስክ ምልከታ ያካሄደው ቋሚ ኮሚቴው፣ ከኦሞ ኩራዝ የሥራ ኃላፊዎች ጋር የመግቢያ ውይይት ካከናወነ በኋላ ከስኳር ፋብሪካው ሠራተኞች ጋር ተወያይቷል ተብሏል።

ከፋብሪካው ሠራተኞች ጋር በተደረገው ውይይት፣ ፋብሪካው ትርፋማ እና ውጤታማ እንዲሆን የሠራተኞች ሚና ላቅ ያለ መሆኑን የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና ጠቁመው፣ በቀ የሸንኮራ አገዳን ለማምረት የሚያስችል ሥራን ለመሥራት ብሎም ከፋብሪካው ምርታማነት ጋር በተያያዘ ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ኃላፊነትን ተቀብሎ ጥናት በማድረግ መሥራት ይገባል ብለዋልም ተብሏል። የኦሞ ኩራዝ ቁጥር ሦሥትን የስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያቀረቡት ኃላፊው አቶ ሀብታሙ አየለ፣ መሠረተ ልማቶችን በማስፋፋት በሸንኮራ አገዳ ተከላ ሥራ እንቅስቃሴ 2600 ሄክታር ለመሸፈን ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ወደ ሌላይኛው የአገሪቷ ስኳር ፋብሪካ መተሐራ የተጓዘው ይኸው ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ስለሺ ኮሬ፣ የአገሪቱን ኢንዱስትራላይዜሽን ለማረጋገጥ እና ስኳር ፋብሪካዎች የተሻለ ምርት ማምረት እንዲችሉ ዘመናዊ ግብርና የላቀ አስተዋፅኦ እንዳለው አስገንዝበዋል ተብሏል። ምክትል ሰብሳቢው አክለውም፣ በዚኽ ሂደት ዘርፉ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ ተቋማዊ ማሻሻያ ከተደረገባቸው ተቋማት አንዱ እንደመሆኑ መጠን የፋብሪካውን አጠቃላይ የዕምርታ ደረጃን ከመበልፀግ ጉዞ ጋር በተናበበ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን በተጨባጭ ለመፈተሽ የታመነበት እንደሆነ መናገራቸው ተዘግቧል።

ወደ ሦሥተኛው ወንጂ ስኳር ፋብሪካ ተጉዘውም የተቋም የመስክ ምልከታ ያደረጉት የዚኹ ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የፋብሪካውን የምርት መጠን ለመጨመር እየተከናወኑ ያሉ የኮንትራት እርሻ ሥራዎችን ተግባራዊ ማድረጉ፣ በራስ አቅም የማሽን ጥገና ሥራዎች እየተከናወኑ መቀጠላቸው የሚበረታታ መሆኑን በእኚኹ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ስለሺ ኮሬ አማካኝነት አፅንዖት መስጠቱን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

የወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ሥራ አስኪያጅ አቶ ሰለሞን በቀለ በበኩላቸው፣ በወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ በተለይ ከ2013 ዓ.ም. እስከ 2016 ዓ.ም. በተለያዩ ክፍተቶች የተነሳ የምርት ማሽቆልቆል ተከስቶ እንደነበር ገልፀዋል ተብሏል። ይኽንንም ለመፍታት ተቋማዊ ማሻሻያ በማድረግ እንዲኹም የፋብሪካውን የማምረት አቅም ከፍ ለማድረግ ከሸንኮራ አገዳ አምራች ገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ጋር የኮንትራት እርሻን በድጋሚ በማስጀመር እና ተቀናጅቶ መሥራት በመቻሉ ተጨባጭ ውጤቶች መመዝገብ መጀመራቸውን በዚያ ላገኟቸው የቋሚ ኮሚቴው አባላት ማብራራታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ጠቅሷቸዋል።



*የወንጂ ስኳር ፋብሪካው ውይይት በከፊል፤*

## 4.2.2 የመስክ ጉብኝቶች

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በወርኃ ጥርም ወደተለያዩ የአገሪቷ ክልሎች በ'የቋሚ ኮሚቴዎቻቸው አማካኝነት የመስክ ምልከታዎችን ከውነዋል። በዚኽም፣ ከዋና ከተማዋ አዲስ አበባ አንስቶ እስከ ኦሮሚያ፣ ከቤንሻንጉል/ጉምዝ እስከ አፋር፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እስከ ሲዳማ ባሉት ክልሎች ውስጥ የሚገኙ

የተለያዩ የየክልሎቹን እንቅስቃሴዎች በተጠሪዎቹ ቋሚ ኮሚቴ አባላት በኩል በአካል በመገኘት ገምግመዋል።

በዚኹ ሽፋን በሰጠነው የዓመቱ አምስተኛ ወር ከተጎበኙት ክልሎች በጊዜ ምጣኔ ቀዳሚው የሆነችው **ቤንሻንጉል/ጉምዝ** ስትሆን፣ በክልሉ በኹሉም የስፖርት ዘርፍ ታዳጊዎችን ለማብቃት የተሰሩት ሥራዎች አበረታች መሆናቸውን በእንደራሴዎቹ

ምክር ቤት የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መግለጡ ተዘግቧል። ቋሚ ኮሚቴው በአሶሳ ዞን በባምባሲ እና በአብርሃሞ ወረዳዎች በሚገኙ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች እና የወጣቶች ማዕከላት የመስክ ምልከታ ሲያደርግ፣ ወጣቶችን ከማብቃት እና የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች ይዞታ እንዲኖራቸው የአመራሩ እና የባለሙያው ቁርጠኝነት ለስፖርቱ ዘርፍ የተሰጠውን ትኩረት ቋሚ ኮሚቴው አድንቆ፣ ይበልጥ ለማጠናከር እና የሚሰበሰበውን ሀብት በአግባቡ ለመምራት የስፖርት ምክር ቤት ጉባኤ በክልሉ ባሉ ኹሉም ወረዳዎች ማካሄድ እንደሚገባ አመላክተዋል ተብሏል።

በዚኽ ወር ክልሏ የተጎበኘችው በተጠቀሰው ቋሚ ኮሚቴ ብቻም ሳይሆን፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በሌላይኛው የንግድ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነትም ነበር። ቋሚ ኮሚቴው የመስክ ምልከታውን ያካሄደው በኢንቨስትመንት፣ ንግድ እና ቱሪዝም ዘርፍ በግማሽ ዓመቱ የተከናወኑት ተግባራት በተያዘላቸው ጊዜ መሠረት የኅብረተሰብን ተጠቃሚነት ሊያረጋግጥ በሚቻል መልክ ስለመፈፀማቸው የቀረቡ ሪፖርቶችን መሠረት በማድረግ ነበርም ተብሏል። በዚኽም የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዮሐንስ መስፍን፣ ክልሉን የመዋዕለ-ንዋይ መዳረሻ ለማድረግ እየተሰራ ያለው ሥራ ለአገር ኢኮኖሚ

እድገት ከፍተኛ አበርክቶ እንዳለው ተናግረው፣ ክልሉ ካለው የተፈጥሮ እና የሰው ሐብት አንጻር የበለጠ ሊሰራ እንደሚገባ ማሳሰባቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። የክልሉ የኢንቨትመንት ቢሮ ኀላፊው አቶ አመንቴ ገሺ በበኩላቸው፣ ከታላቁ ሕዳሴ ግድብ መጠናቀቅ ጋር ተያይዞ የክልሉ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት መነቃቃት እያሳየ መሆኑን ለቋሚ ኮሚቴው አባላት ጠቅሰውላቸዋል ተብሏል።

በዚኹ ወር የመስክ ምልከታ ከተደረገባቸው ክልሎች መካከል **አማራ ክልል** ይገኝበታል። ወደ ክልሉ መቀመጫ ባሕር ዳር ከተማ የተጓዙት በምክር ቤቱ የከተማ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን፣ ኮሚቴውም በባሕር ዳር እና በዙሪያዋ የሚገነቡ የመሠረተ ልማት አውታሮችን ተዘዋውሮ በመመልከት ከክልሉ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ጋርም ውይይት አድርጓል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው አባል የተከበሩ ዘላለም መላኩ፣ በከተማዋ የሚሰሩ የኮሪደር ልማቶች በተቻለ መጠን በቀጣይ አገሪቱን የሚረከቡ ወጣቶች እና ታዳጊዎች በአካል እና በሐሳብ ጠንካራ እንዲሆኑ የሚያስችሉ በቂ የስፖርት ማዘውተሪያዎች እና የማንበቢያ ቦታዎችን ማካተታቸውን ማረጋገጥ ይገባል ብለዋል ተብሏል።

የተከበሩ ዘላለም አክለውም፣ ኅብረተሰቡ በሚያደርጋቸው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ደኅንነቱ ተጠብቆ በነጻነት እንዲንቀሳቀስ በከተማዋ የሚሰሩ መሠረተ ልማቶች ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች በጥምር የያዙ መሆን አለባቸውም ብለዋል። የከተማዋ ከንቲባ አቶ ጎሹ እንዳላማው በበኩላቸው፣ በአኹኑ ወቅት በከተማዋ ደረጃውን የጠበቀ እና የኮሪደር ልማት ልኬት የያዙ ከ17.5 ኪ.ሜ. በላይ የሚሆኑ የኮንክሪት አስፓልት መንገዶች

በመጠናቀቅ ላይ እንዳሉ ለኮሚቴው አባላት አብራርተዋል። ከዚያ ባለፈም፣ ለረጅም ዓመታት የግንባታ ሥራው ተቋርጦ የነበረው የባሕር ዳር የቄራ ድርጅት፣ የክልሉ ምክር ቤት በሰጠው ልዩ አቅጣጫ መሠረት የግንባታ ሂደቱ ተጀምሮ በመጠናቀቅ ላይ እንደሚገኝም ተናግረዋል ተብሏል።

ወደ አማራ ክልል መቀመጫዋ የሄዱት ከላይ የተጠቀሱት የከተማ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ብቻም ሳይሆኑ፣ የኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ጭምር መሆናቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ይጠቁማል። በባሕር ዳር እና አካባቢው የሚገኙ አምራች ኢንዱስትሪዎችን የተመለከቱት የዚኹ ቋሚ ኮሚቴ አባል እና የቡድኑ አስተባባሪ የተከበሩ በጋሻው ተክሉ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የአገርን ምርት ለማሳደግ እና የውጭ ንግድ ሚዛንን ለመጠበቅ ዓይነተኛ ሚና ስላላቸው ዘርፉን በመደገፍ መዋዕለ-ንዋይን መሳብ እንደሚገባ አብራርተዋል ተብሏል።

የአምራች ኢንዱስትሪዎች እና የዩኒቨርሲቲዎች ትስስር ዐዋጅ መፅደቁን ያነሱት የቋሚ ኮሚቴው ሌላይኛው አባል የተከበሩ ተስፋሁን ሲሳይ፣ ዘላቂ የኢኮኖሚ ሽግግር ለማምጣት አምራች ኢንዱስትሪዎች እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በቅንጅት መሥራት እንደሚገባቸው መናገራቸውን ዘገባው ጠቅሷቸዋል።

በበጀት ዓመቱ አምስተኛ ወር፣ የመስክ ጉብኝት ከተደረገባቸው የከተማ መሥተዳድሮች መካከል እንደማሳያነት ዋና ከተማዋ ትገኝበታለች። በ**አዲስ አበባ** ጉለሌ ክፍለ-ከተማ የሄዱት በምክር ቤቱ የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ሲሆኑ፤ 'ነርሱም በወረዳ 7 ሽንኮራ ቁጥር ኹለት በማኅበር ተደራጅተው እያለሙ ያሉ የሴቶች የከተማ ግብርና ሥራዎችን ተመልክተዋል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው አባል እና የቡድኑ አስተባባሪ የተከበሩ ወ/ሮ እታፈራሁ ሞታ፣ ሴቶችን ኹለንተናዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በየደረጃው ያሉ ምክር ቤቶች መደገፍ እና ማብቃት እንዳለባቸው አሳስበዋል ተብሏል። አስተባባሪዋ አክለውም፣ ሥራ የለም ከሚል አስተሳሰብ ወጥተው እናቶች የከተማ ግብርናን ለማስፋፋት እና በዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን እያደረጉት ያለው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ጠቅሰዋል። ከካርታ እና ከመሬት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ ያለውን ችግር በየደረጃው ያለ አመራር ዘላቂ መፍትሔ መስጠት እንዳለበት ያሳሰቡት ደግሞ ሌሎይኞቹ የቋሚ ኮሚቴው አባላት መሆናቸው ተጠቅሷል።



*የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት በአዲስ አበባ ጉብኝታቸው ወቅት፤*

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ የከተማ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የመንገድ ደኅንነት እና መድን ፈንድ አገልግሎት የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ የጀመራቸውን ሥራዎች አጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ

ያስገነዘበበት የ**ኦሮሚያ**ው የመስክ ምልከታም የወሩ አንዱ ማሳያ ክንውን ነበር።

ቋሚ ኮሚቴው፣ በመንገድ ደኅንነት እና መድን ፈንድ አገልግሎት የኦሮሚያ ትራንስፖርት ኤጀንሲ ዘርፉን በማዘመን የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ የሚያከናውናቸውን ተግባራት በመስክ ምልከታ አረጋግጧልም ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ፕሮፌሰር መሐመድ አብዱ፣ ተቋሙ በትራንስፖርት ዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ እየሰራ ቢሆንም፣ ለአሽከርካሪዎች እና ለማኅበረሰቡ በተፈጠረው ግንዛቤ ልክ የትራፊክ አደጋው በሚፈለገው መልኩ ሊቀንስ አለመቻሉ ሌላ ጥናት የሚሻ ጉዳይ እንደሆነ አስገንዝበዋልም ተብሏል።

የኦሮሚያ ክልል ትራንስፖርት አጀንሲ የትራፊክ አደጋን በመቀነስ ዘመናዊ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያከናውናቸው ተግባራት በአዎንታዊ የሚታዩ መሆናቸውን የጠቀሱት ደግሞ ሌሎቹ የቋሚ ኮሚቴው አባላት ነበሩ። የኦሮሚያ ክልል ትራንስፖርት ኤጀንሲ ዋና ሥራ አሥፈጻሚው ዳንኤል ቸርነት በበኩላቸው፣ እንደ አገር አኹን ባለው ነባራዊ ኹኔታ ከ1.7 ሚሊየን በላይ ተሽከርካሪዎች የሚገኙ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ 68 በመቶ የትራፊክ አደጋ የሚደርሰው በአሽከርካሪዎች ብቃት ማነስ እንደሆነ በጥናት መረጋገጡን ላገኟቸው የቋሚ ኮሚቴው አባላት አብራርተውላቸዋል።

በዚኽች የእንደራሴ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ጥር ወር፣ የመስክ ምልከታ ከተደረገባቸው ክልሎቹ ሌላይኛው አዲሱ የፌዴሬሽን አባሉ **ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ** ሲሆን፤ ወደዚያ ክልል የደረሱትም በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ነበሩ ተብሏል።

በክልሉ ቢሮ በተካሄደው የመግቢያ ውይይት የክልሉን ርዕሰ መሥተዳድር ዶ.ር. ኢ/ር ነጋሽ ዋጌሾን ጨምሮ የሚመለከታቸው የቢሮ ኃላፊዎች ተገኝተዋል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሪት ፈቲያ አሕመድ ከክልሉ አመራሮች የተገኘው ማብራሪያ ትኩረት የሚሰጣቸው ዘርፎችን ለይቶ የመስክ ምልከታውን ለማካሄድ የሚያስችል መሆኑን እና በመጨረሻም በየደረጃው ላለ አመራር ግብረ መልስ የሚሰጥ መሆኑ አመላክተዋል ተብሏል።

የክልሉ ርዕሰ መሥተዳድር በበኩላቸው፣ ክልሉ በራሱ አቅም የሚያከናውናቸው የንጹሕ መጠጥ ውኃ፣ የመስኖ፣ የቆላማ አካባቢ የመሠረተ-ልማት እና የአካባቢ ጥበቃ ፕሮጀክቶች መኖራቸውን ገልጸው፤ በፌደራል መንግሥት በጀት ተጀምረው የተጓተቱ ፕሮጀክቶች በተለይም የቦንጋ ከተማ የንጹሕ መጠጥ ውኃ እና የሻርማ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ከፍተኛ የሕዝብ ቅሬታ ያለባቸው በመሆኑ የምክር ቤቱን ትኩረት ይፈልጋሉ ብለዋል ተብሏል።



*የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዋ የተከበሩ ወ/ሪት ፈቲያ አህመድ፤*

በወርኃ ጥር በእንደራሴዎቹ ከተጎበኙት ክልሎች መካከል፣ ሩቋ የ**አፋር** ክልል ትገኝበታለች። ወደ ክልሉ የዘለቁት በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ሲሆኑ፤ ቋሚ ኮሚቴው የክልሉን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ወ/ሮ አሲያ ከማልን ጨምሮ ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት የመስክ ምልከታውን አስመልክቶ ውይይት ማድረጉ ተዘግቧል።

የቋሚ ኮሚቴው የመስክ ቡድን አስተባባሪ የተከበሩ ወ/ሮ አቡኔ ዓለም፣ ቋሚ ኮሚቴው በሚከታተላቸው የዲሞክራሲ ተቋማት በበጀት ዓመቱ የታቀዱ ዕቅዶች እና ግቦች ተግባራዊነታቸውን ካረጋገጠ በኋላ አስፈላጊውን የማስተካከያ አቅጣጫ እንደሚያስቀምጥ መናገራቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል። የክልሉ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ወ/ሮ አሲያ ከማል በበኩላቸው፣ ቋሚ ኮሚቴው በእነዚህ ተቋማት የሚያደርገውን የድጋፍ እና የክትትል ሥራ በቀጣይ ክልሉ ከተቋማቱ ጋር ለሚኖረው ቅንጅታዊ አሰራር ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን አንስተው፤ ተቀራርቦ በመሥራትም የክልሉን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ተግባራትን አጠናክረው እንደሚያስቀጥሉ ገልፀዋል ተብሏል።



*የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው አባላት በአፋር የመስክ ጉብኝታቸው ወቅት፤*

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ከጎበኟቸው ክልሎች መካከል **ሲዳማ** አንዷ ስትሆን፣ ወደ ክልሏ ከተማ አለታ ወንዶ የሄዱትም በምክር ቤቱ የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት እንደነበሩ ተጠቅሷል።

በከተማይቱ የሚገኘውን የባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትን ከጎበኙ በኋላ የምልከታ አስተያየታቸውን የሰጡት የቋሚ ኮሚቴው አባል እና የቡድኑ መሪ የተከበሩ ወ/ሮ የሺሐሳብ ጸጋው፣ ባህላዊ የቆጮ ዝግጅት ለእናቶቻችን እና ለሴቶች ከፍተኛ ድካም የሚጠይቅ መሆኑን ጠቁመው፣ ኢንስቲትዩቱ ባደረገው ድጋፍ ይኸንን ችግር ሊቀርፍ የሚችል ዘመናዊ የቆጮ መፋቂያ ቴክኖሎጂ ተሰርቶ ሥራ ላይ ማዋሉን ገልጸዋል ተብሏል።



*የአለታ ወንዶው ውይይት በከፊል፤*

አገራችን በተፈጥሮ ጸጋዎች የበለፀገች መሆኗን የገለጹት የቡድኑ መሪ፣ ለምግብነት እና ለመድኃኒትነት የሚያገለግሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን በምርምር በመለየት ማኅበረሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን በኢንስቲትዩቱ የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው አመልክተዋል። የባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ፕ/ር ካሳሁን ተስፋዬ በበኩላቸው፣ እንሰት ከ25 ሚሊዮን

በላይ ሕዝብ ለምግብነት እንደሚጠቀም ጠቅሰው፣ ባለፉት ዓመታት በእንሰት ላይ በቂ የጥናት እና ምርምር ሥራ እንዳልተካሄደ ግን መናገራቸው ተዘግቧል።

## 5. የፓርላማ ዲፕሎማሲ

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በወርኃ ጥር ሣምት ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲዎችን ከውነዋል። በቀዳሚነትም፣ በምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና የሠላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ተቀማጭነታቸው በኢትዮጵያ ከሆኑት **የኢራን አምባሳደር ጋር** ውይይት ማድረጉ ተዘግቧል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ በኹለቱ አገራት መካከል ከ75 ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ጠንካራ የዲፕሎምሲ ግንኙነት መኖሩን ጠቁመው፣ ይኽም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልፀዋል ተብሏል። ኹለቱ አገራት ፓርላመንታዊ ሥርዓት የሚከተሉ እንደመሆናቸው፣ ይኽን ኹለትዮሽ ግንኙነት በተለያዩ መስኮች በማጎልበት በጋራ እንደሚሰሩም ሰብሳቢው አክለዋል።

በኢትዮጵያ የኢራን አምባሳደር አሊ አክባር ረዛኢ በበኩላቸው፣ በኢራን እና በአካባቢዋ ያለውን አኹናዊ ኹኔታ በተለይም ባለፉት ሳምንታት ኢራን የነበረችበት ሁነት ምን እንደሚመስል ለኮሚቴው አባላት በዝርዝር አስረድተዋል። አምባሳደሩ የኢትዮጵያ እና የኢራን ግንኙነትን በይበልጥ በማጠናከር በትምህርት፣ በጤና እና በቴክኖሎጂ ዘርፎች በትብብር እንደሚሰሩም ተናግረዋል ተብሏል።



*የውጭ ግንኙነት እና የሠላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው አባላት ከኢራኑ አምባሳደር ጋር፤*

ኹለተኛው የወሩ የእንደራሴዎቹ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲም የተከናወነው በዚኹ ቋሚ ኮሚቴ በኩል ሲሆን፣ ኮሚቴውም በኢትዮጵያ **የደቡብ ኮሪያ ሪፐብሊክ አምባሳደር** ከሆኑት ጂ ያንግ ካንግ ጋር ተወያይቷል ተብሏል።

ኹለቱ አገራትም በመካከላቸው ያሉትን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች አጠናክረው እንዲሚያስቀጥሉ መወያየታቸው ተጠቅሷል። 183 አባል አገራትን አቅፎ የያዘውን፣ ኢንተር ፓርላመንታዊ ኅብረትን በፕሬዝዳንትነት ለመምራት በሚደርገው ውድድር ኢትዮጵያ ለደቡብ ኮሪያ ድጋፏን እንድታሳይ አምባሳደሩ ጠይቀዋል ተብሏል። የኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዲማም፣ ኢትዮጵያ በፕሬዝዳንታዊው ምርጫ ለደቡብ ኮሪያ አስፈላጊ ድጋፏን እንደምታሳይ ለአምባሳደሩ ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።



*በኢትዮጵያ የደቡብ ኮሪያ ሪፐብሊክ አምባሳደሩ ጂያንግ ካንግ እና የውጭ ግንኙነት እና የሠላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፤*

ሦሥተኛው የወሩ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲም የተከወነው በዚኹ የእንደራሴዎቹ የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ሲሆን፤ ኮሚቴውም የጀርመን ፓርላማ ልዑካንን በምክር ቤቱ ተቀብሎ አነጋግሯል ተብሏል።

በኹለቱ አገራት መካከል ያለው ረዥም ዘመናት ያስቆጠረ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም በውይይቱ ተገልጿል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ በኹለቱ አገራት ፓርላማዎች መካካል ያለው ግንኙነት የአገራቱን የሕዝብ ለሕዝብ ትስስር የሚያጎለብት በመሆኑ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በአካባቢው ያሉ ጎረቤት አገራት ሰላማዊ እና የተረጋጉ እንዲሆኑ የበኩሏን በመወጣት ላይ እንደምትገኝም ገልጸው፣ ከአካባቢው አገራት በተለያዩ ግጭቶች እና ምክንያቶች የተፈናቀሉ ከ 1 ሚሊዮን በላይ ስደተኞችን ማስጠለሏን ለልዑካን ቡድኑ አስረድተዋል ተብሏል። የልዑክ ቡድኑ መሪ የተከበሩ ዴሪያ ቱርክ ናችባውር በበኩላቸው፣ ጀርመን ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ዲፕሎማሲያዊ ትስስር ማሳደግ እና ማጠናከር እንደምትፈልግ መናገራቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል።



*ኮሚቴው እና ልዑኩ በተወያዩበት ወቅት፤*

## 6. እንደራሴዎቹ ስለ'ራሳቸው በ'ራሳቸው

የኢፌድሪ እንደራሴዎች፣ ጥር ወርን ያገባደዱት ሕግጋት በማውጣት አልያም የሥራ አሥፈፃሚ ተቋማትን በመቆጣጠር ብቻም ሳይሆን፣ የሴት እንደራሴዎቹ ኮከስ ከመሰል የክልል እና የከተማ አሥተዳደር ኮከሶች ጋር ውይይቶችን በማድረግ፣ የኮከሱን እና የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት የ2018 በጀት ዓመት የስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርቶችን በመገምገምም ነበር።

በምክር ቤት **የሴት እንደራሴዎቹ ኮከስ፣ ከክልል እና ከከተማ አሥተዳደር ምክር ቤቶች የሴቶች ኮከሶች ጋር የጋራ ስብሰባ** አድርጓል። የኮከሱ የበላይ ጠባቂ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶም፣ ሴቶች በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ እና በምጣኔ ሀብት ዘርፍ በተሟላ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በየደረጃው ያሉት ምክር ቤቶች ሚና ከፍተኛ መሆኑን አስገንዝበዋል ተብሏል።



*የኮከሱ የበላይ ጠባቂ እና ምክትል አፈ ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ*

በኹሉም ዘርፍ የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ኮከሱ ተደራሽነቱን በማስፋት ሲሰራ መቆየቱን ያወሱት የተከበሩ ሎሚ፣ ባለፉት ዓመታት በአንዳንድ የአገሪቷ አካባቢዎች አጋጥሞ በነበረው የፀጥታ ችግር ምክንያት የተሟላ ውይይት ማድረግ አለመቻሉን ገልጸዋል። በዚኹ የጋራ ውይይት ላይ ቀጣዩ ብሔራዊ ምርጫ እና የሴቶች ተሳትፎ ርዕሰ-ጉዳይ መነሳቱ ሲዘገብ፣ በምርጫው የሴቶች ተሳትፎ እንዲጨምር የተመራጭ ሴቶች ኮከስ በትኩረት እንደሚሠራ እኒኹ የኮከሱ የበላይ ጠባቂዋ ጠቅሰዋል ተብሏል። የተከበሩ ሎሚ አክለውም፣ ሴቶች በቀጣዩ ምርጫ በመምረጥ እና በመመረጥ በንቃት መሳተፍ ለአገራዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባታው ወሳኝ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

በወሩ የተከናወነው ሌላይኛው የሴት እንደራሴዎቹ ኮከስ ክንውን፣ **የዚኽን በጀት ዓመት የስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም** አስመልክቶ የተካሄደው የኮከሱ ውይይት ነበር። በዚኽም፣ ኮከሱ ከ2014 ዓ.ም. ጀምሮ በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች በገንዘብ ሲተመን 115 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ማድረጉን የኮከሱ ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ወይዘሮ ዓለሚቱ አበበ ገልጸዋል ተብሏል። ምክትል ሰብሳቢዋ ለጥቀውም፣ ባለፉት ስድስት ወራት በ11 ዩኒቨርሲቲዎች ላይ በሕይወት ክሕሎት ርዕሰ ጉዳይ ላይ እና ለኮከሱ አመራሮች እና ወንድ ተባባሪ አባላት የአቅም ግንባታ ሥልጠና መሰጠቱን አብራርተዋል። በተጨማሪም፣ ኮከሱ ከክልሎች እና ከተለያዩ አገራት ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረጉን ጠቅሰው፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራሮችን በማጠናከር የሴቶችን ኹለንተናዊ ተጠቃሚነት የማጎልበት ሥራዎች መሰራታቸውን ገልጸዋል ተብሏል።

እንደራሴዎቹ በ'ራሳቸው ስለ'ራሳቸው በወሩ ውስጥ ካከናወኗቸው ጉዳዮች ሊጠቀስ የሚችለው ሌላይኛው

ዋነኛ ጉዳይ፣ **የምክር ቤታቸውን ጽሕፈት ቤት የዚኽን በጀት ዓመት የስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም** የገመገሙበት ኩነት ነበር።

በምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የዋና ጸሓፊው ተወካይ ከረዩ ባናታ፣ ይኽንኑ ሪፖርት ማቀረባቸው ሲዘገብ፤ የማሻሻያ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሠ መና፣ ጽሕፈት ቤቱ ባለፉት ስድስት ወራት የምክር ቤቱን ፍላጎት የሚያሳኩ በርካታ የለውጥ ሥራዎች ማከናወኑን ተናግረዋል ተብሏል። ለዚኽ ውጤት መሳካትም ጽሕፈት ቤቱ ብዝሓነትን እና ብቃትን መሰረት አድርጎ የሰራው የሠራተኞች ምደባ ትልቁን ድርሻ እንደሚወስድ የጠቀሱት ሰብሳቢው፣ ለውጡን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባም አሳስበዋል ተብሏል።

ባለፉት ስድስት ወራት የሚዲያ ተደራሽነት፣ የኢቲቪ ፓርላማ ቻናል የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጠናቅቀው ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር ወደ ስርጭት መግባቱንም ሰብሳቢው በስኬትነት ከጠቀሷቸው የጽሕፈት ቤቱ ክንውኖች መካከል ዓይነተኞቹ ናቸው። የማሻሻያ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም በርታ በበኩላቸው፣ ጽሕፈት ቤቱ የሰራው ለውጥ ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮችን መቅረፍ እንደቻለ ተናግረዋል፡ ፡ጽሕፈት ቤቱን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ መተጋገዝን መሰረት ያደረገ አሰራር እንዲኖርም ኹሉም በየደረጃው ኃላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባም ምክትል ሰብሳቢው አሳስበዋል ተብሏል። ሪፖርቱን ያቀረቡት ከረዩ ባናታም፣ በግማሽ ዓመቱ አፈጻጸም በበርካታ ዘርፎች ተጨባጭ ውጤቶች መመዝገባቸውን ማስረዳታቸው ተዘግቧል። አቶ ከረዩ፣ ባለፉት ስድስት ወራት የአገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመን በሚዲያ እና ተግባቦት ሥራዎች፣ በረቂቅ ዐዋጆች፣ በማኅበራዊ ድጋፍ፣ በሎጅስቲክስ እና በሰው ሀብት ልማት እና ተቋማዊ ዝግጅት አበረታች ውጤቶች መመዝገባቸውን መጥቀሳቸውን ከጽሕፈት ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

በጽሕፈት ቤቱ የሙያዊ ድጋፍ ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሓፊው ዶ.ር. ንጉሤ መሸሻ በበኩላቸው፣ ባለፉት ስድስት ወራት የምክር ቤቱን ተልዕኮዎች ለማሳካት በርካታ ስኬቶች መመዝገባቸውን ገልጸዋል፡፡ በተለይም የቴሌቪዥን ቻናል ስርጭት መጀመሩ ምክር ቤቱ የሕዝብ ድምጽነቱን የበለጠ አጉልቶ እንዲያወጣ ትልቅ እድል መፍጠሩን አብራርተዋል ተብሏል።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ዋና ተጠሪ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው አንድነት አድነው በበኩላቸው፣ የማሻሻያ ኮሚቴው በሚያደርጋቸው ክትትሎች በርካታ መሻሻሎች እየተመዘገቡ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ለውጡን ተከትለው የተጀመሩ ሥራዎች ቀጣይነት እንዲኖራቸው ዘመናዊ አሰራርን እና መርህን ተከትሎ መሥራት እንደሚገባ መናገራቸውን መረጃው ጠቅሷቸዋል።



***የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት፣ የበጀት ዓመቱን የስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም ሲገመግም፤***

## 7. እንደራሴዎቹ እና ምርጫ 2018

ተሰናባቹ ስድስተኛው የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ ቀጣዩን 7ኛ ብሔራዊ ምርጫ አስመልክቶ የተለያዩ ሕገ-መንግሥታዊ ኀላፊነቶቹንም በዚኹ ጥር ወር ውስጥ አከናውኗል። ለዚኽ መሰሉ ተቋሚ ኀላፊነቱ ማሳያ የሚሆነው፣ **አገር ዓቀፍ የሕግ አውጪዎች የምክክር መድረክ** ማከናወኑ ነው።

በዚኹ መድረክ ላይ የተገኙት የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ ምርጫው ስኬታማ ሆኖ እንዲጠናቀቅ መንግስት አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ማድረጉን መናገራቸው ተዘግቧል። በምክክር መድረኩም፣ ስለ ምርጫው ቅድመ ዝግጅት እና የምክር ቤቶች ሚና፣ የሕግ ኦዲት እና የፐብሊክ በጀት እና ፋይናንስ ትንተና ጥናት ሰነዶች ላይ ምክክር እንደተደረገባቸውም ከምክር ቤቱ የተገኘው ዘገባ ይጠቁማል።

ከቀጣዩ ምርጫ ጋራ በተያያዘም፣ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምክትል ሰብሳቢ ተስፋዬ ንዋይ፣ በዚኹ አገር ዓቀፍ የሕግ አውጪዎች የጋራ ምክክር መድረክ ላይ “7ኛው አገር አቀፍ ምርጫ ቅድመ ዝግጅት እና የምክር ቤቶች ሚና” በሚል ርዕስ የመወያያ ሰነድ አቅርበዋል። ግንቦት 24 ለሚደረገው ጠቅላላ አገራዊ ምርጫ የምርጫ አሥፈጻሚዎች ምልመላ መደረጉን በዚኹ ሰነዳቸው ላይ የጠቀሱት ምክትል ሰብሳቢው፣ ከጥር አንድ እስከ የካቲት አንድ የእጩዎች ምዝገባ እና ከየካቲት ሰባት እስከ መጋቢት ሰባት ደግሞ የመራጮች ምዝገባ እንደሚደረግ ለመድረኩ ተሳታፊዎች አብራርተዋል።

ለሚደረገው ጠቅላላ ምርጫ በመላ አገሪቷ 50 ሺሕ የምርጫ ጣቢያዎች እንደሚኖሩ የገለጹት አቶ ተስፋዬ፣ እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ 1 ሺሕ 500 መራጮችን ያስተናግዳል ብለዋልም ተብሏል። ግንቦት 24 ላይ ለሚካሄደው ምርጫ 318 ሺሕ የምርጫ አሥፈጻሚዎች እንደሚያስፈልጉ እና የምርጫ ውጤቱም ሠኔ 4 ይፋ እንደሚደረግ አስታውቀዋል። ምክትል ሰብሳቢው፣ ምርጫውን ለማከናወን ዐሥር ቢሊዮን ብር መመደቡንም አያይዘው ገልጸዋል። በትግራይ ክልል ጭምር ምርጫ እንደሚደረግ የጠቀሱት አቶ ተስፋዬ፣ ጉዳዩን በተመለከተ ከክልሉ ጊዜያዊ አሥተዳደር እና በክልሉ ከሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፖርቲዎች ጋር ውይይት መደረጉን ተናግረዋልም ተብሏል።

የኢፌድሪ እንደራሴዎች፣ ከዚኽ መሰሎቹ ክንውኖቻቸው ባለፈ፣ የተለያዩ ክልሎች ለቀጣዩ ምርጭ ያደረጓቸውን ቅድመ-ዝግጅቶችም በ‘የቋሚ ኮሚቴዎቻቸው በኩል የመስክ ምልከታ አድርገዋል። በጊዜ ምጣኔ በቀዳሚነት የተጎበኘው **የአፋር ክልል** ሲሆን፣ ወደ ክልሉ የደረሱት በምክር ቤቱ የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ሲሆኑ፤ እነርሱም ክልሉ ለቀጣዩ ምርጫ የሚያደርጋቸው ቅድመ-ዝግጅቶችን ተመልክተዋል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ እውነቱ አለነ፣ በክልሉ የሚገኘው የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ቅርንጫፍ፣ በአኹኑ ወቅት ትልቅ አገራዊ ኃላፊነት ያለበት እንደሆነ ገልጸው፣ ዜጎች ስለምርጫው ያላቸውን ግንዛቤ በማሳደግ እንዲኹም የሥነ-ዜጋ እና የመራጮች ትምህርት ተደራሽነቱን በማስፋቱ ረገድ በቅድመ ዝግጅቱ ሰፊ ሥራዎች ሊሠሩ ይገባል ብለዋል ተብሏል።

ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ ምርጫው ሰላማዊ፣ ፍትሐዊ እና ዲሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ የሰው ኃይል እና የሚያስፈልጉ ግብአቶች እንዲሟሉ፣ በምርጫው ሂደት

ወጣቶች በበጎ ፈቃደኝነት እንዲያገለግሉ እና በገለልተኝነት እንዲሳተፉ እንዲኹም አካታችነት ላይ የተሰሩ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸውም ሰብሳቢው አክለው መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷል። በኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ የአፋር ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ጠሃ አሊ፣ ምርጫው ሰላማዊ፣ ፍትሓዊ እና ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን የክልሉ ምርጫ ቦርድ ግንዛቤ ከመፍጠር ጀምሮ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቁን ገልፀዋል።

በክልሉ በ1 ሺሕ 6 መቶ 90 የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ምርጫ እንደሚካሄድ የገለጹት ኃላፊው፣ የምርጫ አሥፈጻሚዎች በ32 ወረዳዎች ላይ እንደሚመደቡም ጠቀመዋል። ይኽን ያደመጠው ቋሚ ኮሚቴው፣ ኅብረተሰቡ በራሱ ቋንቋ ግንዛቤ ተፈጥሮለት ካርድ ከወሰደ በኋላ ትክክለኛ ምርጫውን እንዲመርጥ በተለይም የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም ስለምርጫው ግልፅነት መፍጠር እንደሚያስፈልግ የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱን ኀላፊዎች አሳስቧል ተብሏል።



***የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው እውነቱ አለነ በውይይቱ ወቅት፤***

በዚኹ ጥር ወር፣ ከአፋር በተጨማሪ ምርጫውን የተመለከተ የመስክ ምልከታ የተካሄደው **በአማራ ክልል** ሲሆን፤ ወደ ክልሉ የተጓዙትም ከላይ የተጠቀሰው ቋሚ ኮሚቴ አባላት እንደነበሩ ተዘግቧል።

የቋሚ ኮሚቴው የመስክ ቡድን አስተባባሪ የተከበሩ ወ/ሮ አቡኔ ዓለም፣ የሕግ ማዕቀፎች ላይ በተደረገው ማሻሻያ አደረጃጀቱ ውጤታማ መሆኑን በጥንካሬ አንስተው ዜጎች ሕገ-መንግስታዊ መብታቸው ተከብሮ እንዲመርጡ ከማድረግም ባሻገር ምርጫው አካታች እንዲሆን አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል ተብሏል። በሌላ በኩል የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግስት ጎን ሆነው ምርጫው ሰላማዊ፣ ፍትሓዊ እና ዲሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ አስቻይ ሁኔታ ላይ ሊሠሩ ይገባልም ብለዋል።

በኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው ጌታሰው በላቸው በበኩላቸው፣ ቦርዱ በክልሉ ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በመሥራት ላይ እንደሆነ ገልፀው፤ ምርጫው ሰላማዊ፣ ፍትሓዊ እና ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን ቦርዱ ነፃ እና ገለልተኛ ሆኖ እየሰራ እንደሆነ ላገኟቸው የቋሚ ኮሚቴው አባላት ነግረዋቸዋል።



***የቋሚ ኮሚቴው የመስክ ቡድን አስተባባሪ የተከበሩ ወ/ሮ አቡኔ ዓለም፤***

## 8. ሹመቶች

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በወርኃ ጥርም የተለያዩ ሹመቶችን አጽድቀዋል። በምክር ቤቱ 5ኛ ዓመት 11ኛ መደበኛ ስብሰባ ወቅት የተሾሙትም፣ **የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የቦርድ አባላት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንቶች እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞች** ነበሩ።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታው ዶ.ር. ምህረቱ ሻንቆ፣ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን እጩ የቦርድ አባላት ተሿሚዎችን ግለ ታሪክ ባቀረቡበት ወቅት፣ ተሿሚዎቹ በትምህርት ዝግጅታቸው፣ በሥራ ልምዳቸው ለኢትዮጵያ ኹለንተናዊ ለውጥ ጉልህ አስተዋፅኦ ያበረከቱ በመሆናቸው ምክር ቤቱ ሹመታቸውን እንዲያጸድቅላቸው ጠይቀዋል።

በዚኽ መሰረትም ምክር ቤቱ በእጩነት በቀረቡት ዘጠኝ ዕጩዎች ላይ ከተወያየ በኋላ ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የቦርድ ሰብሳቢ እና አባልነት የሚከተሉትን ዕጩ ተሿሚዎች የሹመት ሐሳብ በኹለት ተቃውሞ በአብላጫ ድምጽ አጽድቆታል። **በዚኽም፦የተከበሩ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን በቦርድ ሰብሳቢነት፤ ዶ.ር. መቅደስ ዳባን፣ ዶ.ር. እንደገና አበበን፣ ዶ.ር. አብዱልዋሳ አብዱላህን፣ ዶ.ር. ወርቁ ጋቻናን፣ አቶ ቸሩ ጌታ ገነነን፣ አቶ ጃፋር በድሩን፣ አቶ ጌታቸው ድንቁን እና አቶ የሱፍ ኢብራሂምን** ደግሞ በቦርድ አባልነት መሾሙ ተዘግቧል።

ከዚኽ የብሮድካስቱ ሹመት በተጨማሪም፣ ምክር ቤቱ በዚያው ዕለት በዋለው መደበኛ ስብሰባው፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንቶችን እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞችን ሹመትም አፅድቋል።

የዳኞቹን ሹመትም ያቀረቡት ሚኒስትር ዴኤታው ሲሆኑ፤ ምክር ቤቱ በቀረቡለት ዕጩዎች ላይ ተወያይቶ የአቶ **ልዑል ካህሳይን እና የአቶ ምትኩ ማዳን** ሹመት ውሳኔ ቁጥር 6/ 2018 አድርጎ በአንድ ድምፀ ተዓቅቦ በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል ተብሏል።በተመሳሳይም ምክር ቤቱ በቀረቡለት 50 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዕጩ ዳኞች ላይ ውይይት ካደረገ በኋላ፣ የቀረቡለትን ዕጩዎች ሹመት የውሳኔ ሀሳብ ቁጥር 7/2018 በማድረግ በአንድ ድምፅ ተዓቅቦ በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል።



*የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታው ዶ.ር. ምህረቱ ሻንቆ፣ ዕጩ ተሿሚዎችን ሲያቀርቡ፤*

## 9. የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታ በሽግግር ፍትሕ፣ በእንደራሴዎቹ ሚና እና ተያያዥ ርዕሰ-ጉዳዮች ዙሪያ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ ከኹለት ዓመታት በፊት አንድ ግዙፍ ፖሊሲ አጽድቆ ነበር። ይኽ የሽግግር ፍትሕ የተሰኘው የበዙ ማኅበረ-ፖለቲካዊ እና ተቋማዊ ተጽዕኖዎች ያሉት ፖሊሲ፣ ምንም እንኳን በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ካጸደቀው ዋለ አደር ቢልም፣ አልፎም የሽግግር ፍትሕ ትግበራ ፍኖተ-ካርታው ነሐሴ 2016 ዓ.ም. በፍትሕ ሚኒስቴር አማካኝነት ቢዘጋጅም፣ ትግበራው የመዘግየት ኹኔታ ሳይገጥመው አልቀረም። ከዚያ ባለፈም፣ በትግበራው ፍኖተ-ካርታ እንደተቀመጠው፣ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ሊያጸድቋቸው ይገቡ የነበሩ ፖሊሲውን ማስፈጸሚያ የተለያዩ ዐዋጆች፣ ይኽች የእንደራሴ ዕትም እስክትዘጋጅ ድረስ ወደ እንደራሴዎቹ ጠረጴዛ አልደረሱም።

እነሆ ይኽች የወርኃ ጥር የእንደራሴ ዕትምም፣ እኒኽን ርዕሰ-ጉዳዮች ጨምሮ፣ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ይኽን ፖሊሲ እና የትግበራ ፍኖተ-ካርታውን አስመልክቶ ይኖሩበታል ተብለው የሚታመኑትን ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቶች፣ በፖሊሲው እና በአተገባበሩ ዙሪያ ከተለያዩ ወገኖች በተቆርቋሪነት የሚነሱትን ሒሶች፣ ከዚያ ሻገር ብላም የተቋማችንን ወሳኝ ምክረ-ሐሳቦች አካታ ለማተት ትሞክራለች።

### የሽግግር ፍትሕ ሲሉ...

በሰው ልጆች የታሪክ መዘግብት ተሰንደው የምናገኛቸው አያሌ መልካም ነገሮች የመኖራቸውን ያህል፣ በተቃራኒው ደግሞ የሰው ልጆች ግፍ እና በደል ሲፈጽሙ እና ሲያስተናግዱ ክፍለ-ዘመናትን ተሻግረዋል። በዚኽም በተለይ በበደሉ ገፈት ቀማሾች ላይ የሚደርሰው ሰቆቃ እና ሀዘን ሰዎችን ለበቀል እያነሳሳ ሌላ ጥፋት ሲያስከትል ማስተዋልም እንግዳ አይደለም። በዚያው ልክ ሰዎች የደረሰባቸውን ግፍ ለማራገፍ ፍትሕን ሲሹ ሰንብተዋል። እምባቸው የሚታበሰው፣ ቁስላቸው የሚሽረው ለደረሰባቸው በደል ካሳ የሚሆን ፍትሕ ሲያገኙ ብቻ እንደሆነም ያምናሉ።

በርካታ አገራትም በታሪክ ውስጥ ላጋጠሟቸው ስብራቶች የሽግግር ፍትሕን አማራጭ አድርገው በመጠቀም ለችግሮቻቸው መፍትሔ ያበጁሉ። እ.ኤ.አ. በ1970ዎቹ መጀመሪያ በምሥራቅ አውሮፓ እና በደቡብ አሜሪካ ተግባራዊ በተደረገው የሽግግር ፍትሕ፣ በጦርነት እና በግፍ አገዛዝ የተበደሉ አካላት ፍትሕ እንዲያገኙ የተደረገበት መንገድም ለዚኽ ተጠቃሽ ማሳያ ነው። ከዚህ ጊዜ በኋላ የሽግግር ፍትሕ በተለይ በመደበኛ የሕግ ሥርዓት ብቻ መፍትሔ ለመስጠት የሚያስቸግሩ ጉዳዮችን ጭምር በተጠያቂነት፣ በይቅርታ፣ በካሳ እና መሰል ቁስል ሻሪ የፍትሕ ማስፈኛ መንገድ ተደርጎ ተወስዷል።

የሽግግር ፍትሕ ማለት በማኅበረሰቡ ውስጥ በስፋት ለተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ምላሽ የሚሰጥበት አካሔድ መሆኑን ምሁራን ያስረዳሉ። ይኽንን ሂደት ሰላማዊ፣ ኹሉን አካታች እና ተደራሽ ለማድረግ የኹሉም ጥረት እና አጋርነት ቀዳሚ መነሻ ሊሆን እንደሚገባውም

ይገልጻሉ። የሽግግር ፍትሕ በአንድ ጊዜ የሚያልቅ ሳይሆን ጊዜ የሚጠይቅ እና ቀላል የማይባሉ ዓመታትን ሊወስድ የሚችልም ነው። ይኽም ለተበዳዮች ፍትሕ በመስጠት፣ ካሳ በመክፈል፣ የወደሙ ንብረቶችን መልሶ በመገንባት እና በመሰል ሂደቶች ሊፈጸም ይችላል።

የሽግግር ፍትሕ አገራት ከ'ርስ በ'ርስ ጦርነት፣ ከፀብ እና ከመረቀዘ ጥላቻ አዙሪት እንዲወጡ በማድረግ በኩል የማይተካ ሚና እንዳለው የተለያዩ አገራት ተሞክሮዎች ያሳዩናል። ከሰባት ዓመት በፊት በአዲስ አበባ የፀደቀው የአፍሪካ ኅብረት የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ማዕቀፍ፣ የሽግግር ፍትሕ አገራት የተለያዩ መደበኛ እና ባህላዊ ወይም መደበኛ ያልሆኑ የፖሊሲ እርምጃዎችን እና ተቋማዊ አሠራሮችን በመጠቀም የተፈጸሙ ጥሰቶችን፣ ክፍፍሎችን እና አለመመጣጠኖችን ለማስወገድ እና ለደኅንነትም ሆነ ለዴሞክራሲያዊ እና ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ለውጥ ሥርዓት ግንባታ ምቹ ኹኔታዎችን ለመፍጠር የሚደረግ ጠቃሚ እና አስፈላጊ ሂደት እንደሆነ በብዛት ይጠቀሳል።

የሽግግር ፍትሕ በግጭት፣ በጦርነት ወይም ጨቋኝ ሥርዓት በነበረበት ወቅት ለተፈፀመ ጥቃት፣ መጠነ-ሰፊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት እና በደል የተሟላ መፍትሔ መስጠት መቻል ነው። ይኽም በዋናነት ሙሉ ፍትሕ የሚሰጥበትን መንገድ በመዘርጋት ዘላቂ ሰላም፣ እርቅ፣ መረጋጋት እና የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ሥርዓት መገንባት የሚቻልበትን ኹኔታ ይመለከታል።

በኢትዮጵያ ተግባራዊ ሊካሄድ የታሰበው የሽግግር ፍትሕ በአራት ዋና ዋና ምክንያቶች አስፈላጊ መሆኑን ፍትሕ ሚኒስቴር መግለጡ ይታወሳል። አንደኛው ኢትዮጵያ የምትገኝበት አገራዊ አውድ ሲሆን፤ በዚኽም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ አለመረጋጋቶች፣ ግጭት እና የ'ርስ በ'ርስ ጦርነት ተከስቷል። ይኽም ዜጎችን ለሞት፣ ለአካል ጉዳት እና ለመፈናቀል ያጋለጠ መሆኑ በገፊ ምክንያትነት ይጠቀሳል። ለ'ነዚህ ችግሮች ከዚኽ በፊት የተሰጡ ምላሾች ሙሉ አለመሆናቸው የአጥፊዎች እና የተጎጂዎችን ቁጥር ማብዛቱ፣ የበደሎች መደራረብ እና የጥፋቶች ማኅበረሰባዊ ቅርጽ መያዝ በመደበኛው የፍትሕ ሥርዓት እና አካሔድ ፍትሕ መስጠትንም ሆነ ይቅርታ እና እርቅን ማከናወን አላስችል ማለቱ የሽግግር ፍትሕ ትኩረት እንዲሰጠው አድርጓልም ተብሏል።

ኹለተኛው የተሳካ የሽግግር ፍትሕ ለአገረ-መንግሥት ግንባታ ወሳኝ በመሆኑ፣ ማለትም ባለፉ በደሎች ይቅር ለመባባል፣ እርቅ ለማውረድ፣ ሕዝብ ለማቀራረብ፣ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እና ለተፈጸመ በደል እውቅና ለመስጠት አስፈላጊ በመሆኑ ነው። ሦሥተኛው ምክንያት የተሳካ የሽግግር ፍትሕ ሂደት ሳይተገበር የዴሞክራሲ ሽግግርም ሆነ ዘላቂ ሰላም ማስፈን አይቻልም የሚል መሆኑ ተነግሯል። የመጨረሻው በገፊ ምክንያትነት የሚጠቀሰው ሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር እና የሕግ የበላይነትን ለማስፈን የሽግግር ፍትሕ ወሳኝ መሆኑ ነው።

ኢትዮጵያ በነዚኽ ምክንያቶች የሽግግር ፍትሕን ለማስፈን እየሰራች መሆኑ በበርካቶች ዘንድ በአዎንታዊ መልክ ይጠቀሳል። በተለይ የሽግግር ፍትሕን ተግባራዊ ካደረጉ አገራት ተሞክሮ በመውሰድ ለውጤታማነቱ ከተሰራ በ'ርግጥም አይነተኛ መፍትሔ ነው። ከአፍሪካ ደቡብ አፍሪካ፣ ሴራሊዮን፣ ላይቤሪያ፣ ሩዋንዳ፣ ዲሞክራቲክ ሪፓብሊክ ኮንጎ በቅርቡ ደግሞ ጋምቢያ የሽግግር ፍትሕን ለችግሮቻቸው መፍቻነት ከተጠቀሙ አገራት መካከል መሆናቸውን ማስታወስም ያሻል።

## ለመሆኑ ፖሊሲው ምን ይዟል?

የሽግግር ፍትሕ፣ ጉልህ የመብት ጥሰቶች በተፈፀሙባቸው አገራት ተጠያቂነትን ለማስፈን እና ተበዳዮችን ለመካስ ጥቅም ላይ ሲውል ቆይቷል። በአገራችንም የሽግግር ፍትሕ አስፈላጊነት ታምኖበት ፖሊሲ ሲዘጋጅ መቆየቱ የሚታወቅ ነው። ይኸ ፖሊሲ ተጠናቆ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀ ሲሆን፣ ፖሊሲው የያዛቸውን ዋንኛ ጉዳዮች መጥቀስ፣ ሀተታችንን ምልዑ ያደርገዋልና፣ ጥቂት ነጥቦችን ከፖሊስው ውስጥ እንፍለቅቅ።

የፖሊሲው መግቢያ፣ በአገራችን በተለያዩ ዘመናት የተከሰቱ እና የቀጠሉ ተደራራቢ እና ሰፊ የተጎጂ እና የአጥፊ ወሰን ያላቸው የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ የ'ርስ በ'ርስ ግጭቶች፣ ያልጠሩ ትርክቶች እና በደሎችን ለመፍታት የተደረጉ የተለያዩ ሙከራዎችን የሚያብራራ እንዲኹም አኹን ለምን ኹሉን ዓቀፍ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ እንዳስፈለገ የተብራራበት ነው። ፖሊሲው ሦሥት ዋና ዋና ክፍሎችን የያዘ ሲሆን፥ የመጀመሪያው ክፍል ጠቅላላ የፖሊሲ ጉዳዮች የተገጸበት ሲሆን፣ ኹለተኛው ክፍል የፖሊሲ ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች የተተነተነበት ነው። የመጨረሻው ክፍል የመንግስት እና የባለድርሻ አካላት ሚና እና የክትትል እና ድጋፍ ሥርዓት ተብራርተውበታል።

በፖሊሲው ክፍል አንድ ሥር የፖሊሲው ዓላማ በግልጽ የተብራራ ሲሆን፤ ይኸውም የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አውድ መሰረት ያደረገ፣ የተቀናጀ እና የተናበበ የሽግግር ፍትሕ ሂደት የሚመራበት እና የሚተገበርበትን ሥርዓት በመዘርጋት ዘላቂ ሰላም፣ ዕርቅ፣ የሕግ የበላይነት፣ ፍትሕ እና ዲሞክራሲ የሚረጋገጥበትን መደላድል መፍጠር ያለመ መሆኑ ተመላክቷል። ፖሊሲው የሚመራባቸው መርሆዎችም በጥልቀት እና በዝርዝር የተብራሩ ሲሆን፤ ዋና ዋና መርሆዎቹም ሰብዓዊ መብት ተኮር የትግበራ ሂደት፣ ከጥቃት ወይም ከጉዳት መጠበቅ፣ አገራዊ ባለቤትነት፣ አውድ ተኮር የአተገባበር ሥርዓት፣ ተጠያቂነት፣ ኹለንተናዊነት፣ አካታችነት እና አሳታፊነት፣ ሥርዓተ-ጾታ ተኮር አተገባበር፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ እና አገር በቀል የግጭት አፈታት እሴቶችን ጥቅም ላይ ማዋል ናቸው።

በክፍል ኹለት ሥር የፖሊሲው ጉዳዮች እና አቅጣጫዎች የሚል ዋና ርዕስ ያለው ሆኖ አምስቱ የሽግግር ፍትሕ አምዶችን አስመልክቶ ፖሊሲው ተግባራዊ የሚሆንበት አግባብ የተብራራበት ነው። በዚኹ አግባብ የመጀመሪያው የሽግግር ፍትሕ አምድ የሆነው የወንጀል ተጠያቂነት ሥር ዐራት ዋና ዋና ጉዳዮች የታዩ ሲሆን፤ እነዚኽም ምርመራ እና ክስ የሚወሰንባቸው ወንጀሎች፣ ምርመራ የሚከናወንባቸው እና ክስ የሚመሠረትባቸው አጥፊዎች፣ ወንጀል ምርመራ እና ክስ የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት እና የፍርድ ሂደት የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት ናቸው። ከወንጀል ምርመራ እና ክስ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ በሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደት ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እና ከባድ ወንጀሎችን መለየት የሚያስችል ግልፅ መለያ መስፈርት በመዘርጋት ጉልህ በሆኑ ወንጀሎች ላይ ትኩረት ያደረገ የክስ ሂደት ይከናወናል ተብሏል።

በሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደት የወንጀል ምርመራ የሚካሔድባቸው እና ክስ የሚመሰረትባቸው አጥፊዎችን በተመለከተ በጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ላይ ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች ላይ ተግባራዊ ይደረጋል የተባለ ሲሆን፤ በጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰት

ድርጊት የተሳተፉ ነገር ግን ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ የሌላቸው አጥፊዎችን እንደየአግባብነቱ ሌሎች የሽግግር ፍትሕ ስልቶችን በመጠቀም ጉዳያቸው የሚታይበት እና መፍትሔ የሚሰጥበት ሥርዓት እንደሚዘረጋም ተብራርቷል።

የክስ ሥራ የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓትን በተመለከተ አኹን ካለው የወንጀል ምርመራ እና ዐቃቤ ሕግ ተቋም ውጪ በሆነ፣ ነጻ እና ገለልተኛ ሆኖ ራሱን ችሎ በሚቋቋም እና የሕዝብ አመኔታ በሚኖረው አዲስ የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋም አማካኝነት የሚከናወን እንደሆነ በፖሊሲው ላይ ተቀምጧል። የፍርድ ሂደት የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓትን በተመለከተ በነባሩ ፍርድ ቤት ውስጥ የሽግግር ፍትሕ ጉዳዮችን ብቻ የሚመለከት ልዩ ችሎት እንደሚቋቋምም ተቀምጧል።

በሽግግር ፍትሕ ሥርዓት ኹለተኛው አምድ እውነትን ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና የዕርቅ ተግባር ሲሆን፤ በፖሊሲው እውነት የማፈላለግ፣ ይፋ የማውጣት እና የዕርቅ ሥራ በኹሉም ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ በማተኮር የጥሰቶችን መሠረታዊ ምክንያቶች፣ ተከታታይነት፣ ስልታዊነት፣ መጠነ-ሰፊነት፣ ዓይነት እና የጉዳት መጠን በመለየት ተግባራዊ እንደሚደረግ ተነግሯል። እውነትን የማፈላለግ፣ ይፋ የማውጣት እና የዕርቅ ተግባራት ከተጽዕኖ እና ፖለተካዊ ጣልቃ ገብነት ነጻ እና ገለልተኛ ሆኖ በሚቋቋም አዲስ የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነት እንደሚከናወንም በፖሊሲው ላይ በግልጽ ተቀምጧል።

በቅድመ–ኹኔታ ላይ የተመሠረተ ምህረት ሦሥተኛው አምድ ሲሆን ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ ቅድመ-ኹኔታዎችን በተመለከተ የሽግግር ፍትሕን በሚያሳልጥ፣ የሕግ የበላይነት እና ተጠያቂነትን በማያስቀር መልኩ በቅድመ–ኹኔታ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ ምህረት በአግባቡ ተዘርዝረው እና ለምህረት ብቁ የሚያደርጉ ኹኔታዎች ተብራርተው በፖሊሲው ውስጥ ተጠቅሰዋል። የምህረት ተግባር የሚከናወንበት ተቋማዊ ሥርዓት ከእውነት ማፈላለግ፡ ማውጣት እና ከዕርቅ ተግባራት ጋር በተሰናሰለ እና ተመጋጋቢ በሆነ መንገድ የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽኑ ምህረት የመስጠቱን ተግባር በተደራቢነት እንደሚያከነውንም ፖሊሲው አስቀምጧል።

ተግባራዊ የሚደረጉ የማካካሻ ዓይነቶች እና ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮችን በሽግግር ፍትሕ ሂደት ውስጥ አቅምን እና ነባራዊ ኹኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተግባራዊ የሚደረጉ የማካካሻ አይነቶች በዋናነት መልሶ ማቋቋም፣ የማገገሚያ እርምጃዎች፣ ፈውስ፣ የመታሰቢያ እና ማስታወሻ ክንዋኔዎች፣ የጥሰቶችን ሙሉ ሀቅ ማፈላለግ፡ ይፋ ማውጣት እና እውቅና መስጠት እንዲኹም ለተፈጸሙት በደሎች በመንግስት ደረጃ ይፋዊ ይቅርታ መጠየቅ ወዘተ ናቸው። የማካካሻ ሥራን ምህረት ከመስጠት እና ከእውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት እና የዕርቅ ተግባር ጋር በተሰናሰለ መንገድ የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽኑ የማካካሻ ሥራዎችን የሚያከናውን መሆኑን በፖሊሲው ላይ ተብራርቷል።

ተቋማዊ ማሻሻያን በተመለከተ የተቋማዊ ማሻሻያ ሥራ ትኩረት የሚያደርግባቸው ተቋማት በዋናነት በሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ በተሳተፉ ሰዎች፣ የዜጎችን ሰብዓዊ መብት በማክበር ወይም በማስከበር ረገድ ኃላፊነታቸውን ባልተወጡ፣ ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ በሚችሉ አገራዊ እና ክልላዊ የፍትሕ፣ የፀጥታ እና የደኅንነት ተቋማት፣ የሚዲያ ተቋማት፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሰብዓዊ መብትን ከማስከበር አኳያ ኃላፊነታቸውን ባልተወጡ ተቋማት፣ እና ለሰብዓዊ መብት ጥሰት አስቻይ ኹኔታን

በፈጠሩ ሕግጋት፣ ፖሊሲዎች እና አሰራሮች ላይ ቅድሚያ በመስጠት ማሻሻያ እንደሚደረግባቸው በፖሊሲው ላይ በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን፤ የተቋማዊ ማሻሻያ ሥራው ውጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተቀባይነት እና የሕዝብ አመኔታ እንዲኖረው ለማድረግ ነጻ፣ ገለልተኛ እና ብቃት ባለው ተቋም ማለትም በሕግ እንዲቋቋም በማድረግ ሥራው እንደሚመራ ተብራርቷል።

የሽግግር ፍትሕ ተግባራዊ የሚደረግበትን የጊዜ ወሰን በተመለከተም፣ የሽግግር ፍትሕ የጊዜ ወሰን ለወንጀል ተጠያቂነት ዓላማ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ–መንግሥት ከፀደቀበት ከ1987 ዓ.ም. ጀምሮ ያለው የጊዜ ወሰን ተፈፃሚ የሚደረግ ሲሆን፤ ለእውነት ማፈላለግ፣ ዕርቅ ለማስፈን እና ማካካሻ ሥራዎች ዓላማ ጥሰቶች እና ቅራኔዎችን ከመሰረታቸው በማጥራት ለመመርመር፣ ስብራቶች እንዲሽሩ እና እንዲጠገኑ ለማድረግ እና ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት እንዲቻል የሽግግር ፍትሕ ሂደቱ የተፈፃሚነት ወሰን መረጃ እና ማስረጃ እስከተገኘበት ጊዜ ድረስ ይሆናል በማለትም ፖሊሲ አብራርቷል።

በሽግግር ፍትሕ ትግበራ የክልሎች ሚና በተመለከተ ክልሎች በኹለት ዋና ዋና መንገዶች ሚና የሚኖራቸው ሲሆን፤ የመጀመሪያው በአገር–ዓቀፍ ተቋማት የሚከናወኑ ሥራዎችን በማገዝ ላይ ማተኮር፤ ኹለተኛው ደግሞ በአገራዊ ፖሊሲው አጠቃላይ እሳቤዎች እና እሴቶች ላይ በመመስረት ውስን የሽግግር ፍትሕ ሥራዎችን ራሳቸው በባለቤትነት የሚመሩበትን ሂደት የሚመለከት ነው ተብሏል።

በሽግግር ፍትሕ ባህላዊ የፍትሕ ሥርዓቶች ሚናን በተመለከተም፣ ባህላዊ የፍትሕ ሥርዓቶች ያሉባቸውን ክፍተቶች እንዲስተካከሉ በማድረግ በሚተገበረው የሽግግር ፍትሕ ሂደት ውስጥ ከሌሎች የሽግግር ፍትሕ ተቋማት ጋር በመቀናጀት እውነትን በማፈላለግ፣ ዕርቅ በማስፈን፣ በማካካሻ እና ምህረት በመስጠት ተግባራት እንዲኹም ማኅበረሰባዊ ሰላምን ለማስፈን በሚደረጉ ሥራዎች ማዕቀፍ ጉልህ ሚና እንደሚኖራቸው በፖሊሲው ላይ ተብራርቷል።

የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው እና የትግበራ ሂደቱ የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች ማለትም ልዩ ትኩረት ለሚሹ እና ለጉዳት ተጋላጭ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ለሴቶች፣ ለሕጻናት፣ ለወጣቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን እና ለአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ልዩ ፍላጎት እና ጥቅም ትኩረት በሚሰጥ አግባብ እንደሚከናወን በፖሊሰው ላይ ላይ በጥልቅ ተብራርቷል።

በክፍል ሦሥት ሥር የመንግስት እና የባለድርሻ አካላት ሚና እንዲኹም የክትትል እና ድጋፍ ሥርዓት የተመለከቱ ጉዳዮች የተብራሩበት ሲሆን፤ ዋና ዋና ጉዳዮችም በፖሊሲው መሰረት የሽግግር ፍትሕ ሥራዎችን ተግባራዊ የሚያደርጉ ተቋማት በርከት ያሉ በመሆናቸው፣ እነዚኽ ተቋማት እንዲቋቋሙ ኹኔታዎችን ከማመቻቸት አንስቶ ሥራቸውን ሙሉ ለሙሉ እስኪጀምሩ ድረስ ድጋፍ የሚያደርጉ ተቋማት ተግባር እና ኃላፊነት በዝርዝር የተቀመጠበት ክፍል ነው። ከመንግስት ተቋማት በተጨማሪም የባለድርሻ አካላት ሚና እና የፖሊሲው አፈጻጸም፣ ክትትል እና ድጋፍ ሥርዓትም በሰፊው መብራርቱን ተረድተናል።

## ዘገየ ይሆን?

የሽግግር ፍትሕ ሂደቱ አዝጋሚ ነው የሚል ትችት ሲቀርብበት ይስተዋላል። ለሽግግር ፍትሕ ሂደት ከሕግ ረቂቅ ሰነዶች ውጪ ሌሎች ተግባራት በታቀደላቸው ጊዜ

አለመከናወናቸውም አሳሳቢ ነው ሲባል እየተደመጠ ነው። የሽግግር ፍትሕ ሂደትን የሚመራ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ በሚያዝያ ወር 2016 ዓ.ም. በሚኒስትሮች ምክር ቤት መፅደቁ የሚታወስ ነው። ሆኖም፣ በፍትሕ ሚኒስቴር እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች፣ አጠቃላይ ሂደቱ እየተመራ ያለበት አግባብ ለሕዝብ ግልጽ አለመደረጉም ሲጠቀስ ይስተዋላል። ይኽን የመዘገየት ጉዳይም በስፋት የጠቀሰው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ ከጥቂት ወራት በፊት ባወጣው ሪፖርት ነበር።

ኮሚሽኑ በሪፖርቱም፣ የሽግግር ፍትሕን የመተግበር የፖለቲካ ቁርጠኝነት በአገሪቱ ያሉ ግጭቶችን የማስቆም ጥረቶችን ሊያካትት ይገባል ብሏል። ለሽግግር ፍትሕ ትግበራ፣ ለግጭቶች እና የጸጥታ ችግሮች ምላሽ ለመስጠት እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች ውጤታማ አለመሆን አሳሳቢ ተግዳሮት ሆኗል ሲልም አስቀምጧል። ኮሚሽኑ በተለይም የሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ወደ ትግበራ ምዕራፍ ከተሸጋገረ በኋላ የመቀዛቀዝ አዝማሚያ እያሳየ መሆኑ አሳሳቢ ጉዳይ ነው ተብሏል።

የመንግስት የታደሰ ቁርጠኝነት ለሽግግር ፍትሕ ጥረቶች በጥንቃቄ የታቀደ እና በቅደም ተከተል የተደራጀ የተቋረጠው ሂደት ዳግም እንዲጀመር መንገድ ሊከፍት ይገባል የሚሉ ድምጾችም ይደመጣሉ። በግንቦት 2017 ዓ.ም.፣ የኢትዮጵያ ፍትሕ ሚኒስቴር ዋና ዋና የሕግ ማዕቀፎችን አጠናቆ በነበረበት ወቅት፣ መንግሥት ከሽግግር ፍትሕ ይልቅ ለብሔራዊ ምክክር ቅድሚያ ሊሰጥ ይችላል የሚል ግምት ተፈጥሮ ነበር።

የምክክር ሂደቱ በቀጣዩ የካቲት ወር እንዲጠናቀቅ ታቅዷል፤ ይኽም ህኦነው፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በጸደቀው የአንድ ዓመት የጊዜ ማራዘሚያ ምክንያት መሆኑ ይታወሳል። የሽግግር ፍትሕ ሂደቱ መዘግየቱ፣ በአንዳንድ ታዛቢዎች ዘንድ ሽግግር ፍትሕን እንደ ራሱን የቻለ እና አስፈላጊ የሰላም ግንባታ ሂደት ሳይሆን፣ ከምክክሩ የሚከተል የውሳኔ ሐሳብ አድርገው እንዲመለከቱት ሳያደርግም አልቀረም። ሆኖም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ ጥቅምት 18 ቀን 2017 ዓ.ም. ለእንደራሴዎቹ ሲናገሩ፣ የኢትዮጵያ የሰላም ግንባታ በየሽግግር ፍትሕ ጭምር የሚጸና መሆኑን መናገራቸው የዘገየ ለሚለው ድምጽ የተሰጠ ምላሽ ተደርጎ ሊቆጠርም ይችላል።

'ርሳቸው እንዳሉት፣ የሽግግር ፍትሕ ያለፉ ግፎችን ለመፍታት የታለመ ሲሆን፤ ብሔራዊ ምክክሩ ደግሞ አወዛጋቢ በሆኑ የመንግሥት አሥተዳደር፣ የመንግሥት እና የአገር ግንባታ ጉዳዮች ላይ ስምምነት ላይ ለመድረስ ያለመ ነው። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረውን ጽንሰ ሐሳባዊ ግልጽነት የሰጠ ሲሆን፤ የሽግግር ፍትሕ በኢትዮጵያ የሰላም ግንባታ ማዕቀፍ ውስጥ ማዕከላዊ ምሰሶ እና ራሱን የቻለ ሂደት መሆኑን አረጋግጧል። ይኽም የሽግግር ፍትሕ የምክክሩ ውጤት ነው የሚሉ ቀደምት ግምቶችን ውድቅ አድርጓል የሚል ዕምነት በተቋማችን ጭምር እንዲያዝ መሆኑን ሳንጠቅስ አናልፍም።

## ከሥርዓተ- ጾታ አንጻርስ?

ይኽን የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ሰነድ እና ይተገበራል የተባለውን ፎኖተ-ካርታ አስመልክቶ፣ አንድ ዋንኛ ርዕሰ-ጉዳይን ሳናነሳ ማለፍ አያሻንም፤ ይኸውም፣ ፖሊስውንም ሆነ የትግበራ ሰነዱን ከሥርዓተ-ጾታ አኳያ በጥቂት ነጥቦች ለማንጸር መጣር ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚሰነዘሩ አድሎአዊ ድርጊቶች እና አመለካከቶች ለሴቶች ሕዝባዊ ተሳትፎ ዋና እንቅፋት ከመሆናቸው ባለፈ፣ በዚያም የተነሳ መብቶቻቸው እንደሚጣሱ የበዙ ጥናቶች ያመለክታሉ። እኒኽ ጥናቶች እንደሚጠቅሱት፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ወንድ የፖለቲካ መሪዎች የሴቶችን የፖለቲካ አመራር በተመለከተ የሴቶች ተሳትፎ እና ውጤታማነት ላይ አሉታዊ አመለካከቶች ሲኖራቸው፤ በሕግ አውጪ እና በአሥፈጻሚነት ቦታ ላይ ያሉ ሴት የፖለቲካ መሪዎች ደግሞ ሴቶች በመንግስት እና በፖለቲካ አመራር ውስጥ ስለሚኖራቸው ተሳትፎ የበለጠ አዎንታዊ አመለካከቶችን ያነጸባርቃሉ።

እነዚኽ አመለካከቶች በተለይም በፖለቲካ እና በማኅበረሰባዊ አመራር ውስጥ የተባዕታይ ፆታ የበላይነትን ከሚያበረታታው ባህል እና ማኅበራዊ ስሪት የመነጩ መሆናቸውም አሌ አይባልም። የኢትዮጵያ ተለምዷዊ አስተሳሰቦች እና ግብሮች ሴቶችን የማኅበረሰብ ወይም የፖለቲካ ተወካይ አድርጎ ከማቅረብ ይልቅ የቤት ውስጥ አገልጋይ ብቻ አድርጎ ወደማየቱ ያዘነብላል። ይኽ የሥርዓተ-ፆታ አድልዎ የተመሰረተው ኅብረተሰቡ ወንዶች የበላይ ውሳኔ ሰጪዎች መሆናቸውን በመቀበሉ ሲሆን፤ ሴቶች ብዙውን ጊዜ ጥገኛ እና ታዛዥ ሆነው ስለሚታዩ የፖለቲካ ተሳትፏቸው እና ተጽዕኖቸውም ውስን እንዲሆን አድርጎታል።

በሽግግር ፍትሕ ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ አመለካከትን ማካተት መሠረታዊ ፍትሓዊነትን እና የሰብዓዊ መብቶች መከበርን እንደማረጋገጥ ይወሰዳል። ማንኛውም የሽግግር ፍትሕ ሥርዓት ሥርዓተ-ፆታን በማካተት፣ በሂደቱም ውስጥ በመጠቀም፣ እንዲኹም ፖሊሲዎችን በመቅረፅ እና በማስፈፀም የሴቶችን እኩል ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ያስችላል ተብሎ በብዙዎች ይታመናል።

ይኽ አካሔድም ገንቢ ብቻ ሳይሆን ሴቶች በግጭቶች እና በፍትሕ እጦት ጭምርም ይበልጥ ተጎጂ በመሆናቸው አጅጉን አስፈላጊ ያደርገዋል። በመሆኑም ሴቶችን ከሽግግር የፍትሕ ሂደት ማግለል የኹሉንም ተጎጂዎች ፍላጎት በበቂ ኹኔታ ምላሽ መስጠት ካለማስቻሉ ባለፈ፣ ለሰፊው የኅብረተሰብ ለውጥ የበኩሉን አስተዋጽዖ ስለማያደርግ ለስኬታማነቱ እንቅፋት ይሆናል። በኅብረተሰብ ውስጥ በወንዶች እና በሴቶች መካከል ፍትሓዊ የሥልጣን እና የመብት ክፍፍል አለመኖሩን በመገንዘብ የሥርዓተ-ፆታ ሽግግር ፍትሕ ተገቢ የሆኑትን ዘዴዎች መከተል ይጠይቃልም የሚያስብለው ለዚኹ ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ በእያንዳንዱ የፖሊሲ ቀረፃ እና ትግበራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ፣ እንደ ሴቶች ያሉትን ለዘመናት የተገለሉ ወገኖችን ድምጽ፣ ፍላጎት እና መብት በማካተት እውነተኛ ፍትሕ እንዲሰፍን ማድረግ ለሌላ ትውልድ የሚተው ግብር አይመስለንም። የሥርዓተ-ፆታ አመለካከትን ወደ ሽግግር ፍትሕ ማካተት ለፍትሓዊነት እና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ፋይዳ አለው።

ለዚኽም በዋንኛ ምክንያትነት መጥቀስ የሚያሻን፣ ሴቶች በፖሊሲ አወጣጥ እና ትግበራ ውስጥ ሊኖራቸው የሚገባቸውን እኩል ተሳትፎ ከማረጋገጥ ለጥቃት ተጋላጭነታቸውን እና በግጭቶች ወቅት የሚደርስባቸውን ችግር እና የመብት ጥሰቶች እንዲቀንስ ማገዙ ነው፡፡ ይኽ የሥርዓተ-ፆታ አካሔድ ሰላምን ለማስጠበቅ እና ተደጋጋሚ የጥቃት ዑደቶችን ለማስቆም ሁነኛ ዘዴ ነው ተብሎም ይታመናል። እንዳይደመጡ የተደረጉ ድምፆችን እና ፍላጎቶቻቸውን ለማካተት ዘዴዎችን ማበጀት እንዲኹም

ገሀድ ለሆነው የኃይል ሚዛን አለመመጣጠን ትኩረት መስጠትን ይጠይቃል። እነዚኽ ሥርዓተ-ፆታን ያማከሉ ጥረቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ሴቶች ከብሔራዊ የሽግግር ፍትሕ ሂደቶች መገለላቸውን የሚያስተካክሉ ሲሆን በሴቶች ላይ የሚደርሰውን በደል በማካካስ ለመፍታት ያስችላልም የሚለውንም መጥቀስ ሳያስፈልግ አይቀርም።

ጠንካራ ሥርዓተ-ፆታን ያካተተ የሽግግር የፍትሕ ፖሊሲ በርካታ የመብት ጥሰቶች የሚደርሱባቸውን ሴቶች እና የተገለሉ ቡድኖችን እንደ ልዩ የትኩረት ቡድን እውቅና በመስጠት ሰፋ ያለ አድማስ እንዲኖረው ይጠበቃል። ከሥርዓተ-ፆታ በተጨማሪ ሌሎች ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ኹኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ኹሉን ዓቀፍ፣ ተለዋዋጭ፣ ለአዳዲስ አቀራረቦች ዝግጁ እና ተደራሽ መሆን ይኖርበታል። እነዚኽ አካሔዶች በፖሊሲው ውስጥ መካተት እና መዳበር ይኖርባቸዋል። ተግባራዊነቱን ለመከታተል፣ ለመማማር እና እንደ አስፈላጊነቱም ለማሻሻል የሚረዱ መላዎችን በውስጡ ይሸከማል። በተጨማሪም ኢትዮጵያውያን ሴቶች በየደረጃው ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉበትን አሰራር በመዘርጋት፣ በፖሊሲ ቀረፃ ሂደት ይደርስባቸው የነበረውን መገለል በመቅረፍ ልዩ ልምዶቻቸውን፣ ፍላጎቶቻቸውን እና አቅማቸውን በማዳበር ላይ ትኩረት ማድረግም ይገባዋል። ይኽ አካሔድ በሥርዓተ-ፆታ ኮታ ብቻ የተገደበ ሳይሆን የሴቶችን ውጤታማ ውክልና ለማረጋገጥ በአቅም ግንባታ፣ በልዩ ሥልጠና እና በባለሙያዎች አመዳደብ ምቹ ኹኔታ መፍጠር ይኖርበታል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ኹሉን ዓቀፍ እና ጾታን ያማከለ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ለመዘርጋት እና ተግባራዊ ለማድረግ ግጭቶች እና ጥቃቶች በሴቶች ላይ የሚኖራቸውን ልዩ ትኩረት መገንዘብ አስፈላጊ ነው ብለን እናምናለን። ይኽም ሴቶች የሚያጋጥሟቸውን ልዩ ተጋላጭነቶች እና የመብት ጥሰቶችን በተለይም ግጭት ወለድ ወሲባዊ ጥቃቶችን በተመለከተ ልዩ ትኩረት የሚሻ መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል የሚለው በዚኽ ንዑስ ርዕስ ስር ሳንጠቅሰው ማለፍ አንሻም።

## ሒሳዊ ትችቶችስ ምን ያነሳሉ?

ይኽን የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ አስመልክቶ፣ ከምሁራንም ሆነ ከተለያዩ አገራዊ እና ዓለም ዓቀፍ የመብት ተቆርቋሪ ተቋማት በኩል፣ ሲነሱ የሚስተዋሉ ፖሊሲ እና አተገባበር ተኮር የሙግት ድምጾች መኖራቸውን ተቋማችን ብሪጅ ባደረገችው አጠር ያለ ዳሰሳ ተመልክታለች፤ እናም፣ እነዚህን ሒሳዊ ድጋፍ የሚሰጡት ትችቶችን በተወሰኑ መልኩ መጥቀስ፣ ለቀጣዩ የፖሊስው ትግበራ ኹነኛ ጠቀሜታ አላቸውን በጥቅሉም ቢሆን ብንጠቅሳቸው እና በዋናነትም የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ከታች በመጥይቃዊ መልኩ ጠቅለልን አድርገን ለጠቅስናቸው ነጥቦች ምላሽ የሚሰጡባቸውን አማራጮች ቢሹ ፋይዳቸው ብዙ ነው ብለን እናምናለን። ከዚኽ አኳያም፣ ተቋማችን ብሪጅ ለመሰል ሒሳዊ ትችቶች አግባብነት ያላቸውን ጥናታዊ ምላሾችን በማዘጋጀት አገራዊ ኀላፊነቷን ለመወጣት ዝግጁ እንደሆነችም ማስታወስ ትሻለች፤

* ከተለያዩ የሕግ ባለሙያዎች እና ከምሁራን ከሚቀርበው ትችት ባለፈ በአገሪቱ የሚንቀሳቀሱ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሂደቱን ሲነቅፉ ተደምጠዋል። በመጋቢት 2015 ዓ.ም. የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ አማራጮች ላይ በተደረገ አንድ የውይይት መድረክ ላይም፣ የተወሰኑ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲ

ተወካዮች መድረኩን ረግጠው መውጣታቸው አንዱ ማሳያ ይመስለናል። ፓርቲዎቹ በወቅቱ ከሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ትግበራ በፊት የአገራዊ ምክክር ሊቀድም እና ግጭቶች ሊቆሙ ይገባል የሚል አቋም ይዘውም ነበር። ከዚኽ አንጻር የሚነሳውን የትችች ድምጽ ስንጠቀልለውም፣ ኢትዮጵያ አኹን ያለችበት ኹለንተናዊ አውድ ይኽን ታላቅ ኘሮጀክት ለመፈፀም የሚያስችላት ነው የሚለውኝ የፌደርአል መንግስቱን አቋም የሚጠራጠር ነው። ለምሳሌም፣ በተለይ በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች በተወሰነ መልኩም ቢሆን የታጠቁ ኀይሎች መኖር፣ ማዕከላዊ መንግስቱ የማይቆጣጠራቸው አካባቢዎች በአንዳንድ ቦታዎች መኖርን ታሳቢ ስናደርግ፣ በእርግጥ ይቻላልን ሲሉም ይጠቅይቃሉ።

* በሂደቱ ላይ ሕወሓት አልያም በጥቅሉ የትግራይ ልሂቅ አለመሳተፉ፣ በቀጣይ የፍትሕ ሂደቱን እጅጉን ጎዶሎ ያደርገዋል የሚለውም ሌላይኛው ነው። ከዚኽ በተጨማሪም፣ የትግራይ ክልል ያቋቋመው የዘር ማጥፋት ኮሚሽን ሚና በዚኽ ሂደት ምን ሊሆንስ ይችላል? የሽግግር ፍትሑ ሊመረምራቸው እና ሊፈታቸው ግቡ ካደረጋቸው ወንጀሎች መካከል አንደኛዋ ማዕከል ትግራይ እንደመሆኗ፣ ነገር-ዓለሙ ከፈረሱ ጋሪውን ማስቀደም እይሆንምን? ሲሉም ተቺዎቹ ይጠይቃሉ።

* የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው ሕገ-መንግሥቱ ከፀደቀበት ከ19 87 ዓ.ም. እንደሚጀምር ይናገራል፤ ለምን 1987 የሚሉ በበኩላቸው፣ ይኽ አካሄድ ከ83 እስከ 87 ባሉት ጊዜያት የተፈጸሙትን የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መዘንጋት አይሆንምን? ሲሉ ያነሳሉ። በሃርቫርድ ዩንቨርስቲ አማካኝነት፣ *"ETHIOPIA PEACE & JUSTICE SURVEY"* በሚል ርዕስ የተሰራ አንድ ጥናትም፣ 54% ኢትዮጵያውያን በእነዚኽ ዓመታት ለተፈፀሙት በደሎች ፍትሕ እንደሚፈልጉ መግለፃቸውንም ለትችታቸው ተጨባጭ መነሾ ያድርጉታል።

* የአንዳንድ የሕግ ባለሙያዎች በበኩላቸው፣ የሽግግር ፍትሕን በተመለከተ ረቂቅ ፓሊሲውን የሚያወጣው ፍትሕ ሚኒስቴር፣ ክስ እና ተጠያቂነትን እንዲያሰፍን የሚጠበቀው የፌዴራል ፖሊስ መሆናቸውን በመጥቀስ፣ እነዚኽ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ታላቁን ግብር በትክክል ያስፈጽማሉ ብሎ ማመን ይቸግረናላ ባይ መሆናቸውም የአደባባይ እውነት ይመስለናል።

* ይኽ የሽግግር ፍትሕ ግድ የሚለውን ተጠያቂነት እስከ ላይ ድረስ የሚፈቅድ የፖለቲካ ምህዳር የለም የሚሉ እና ሂደቱ የሚጠይቀውን መንግስታዊ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት የሚጠራጠሩም ብዙዎች ናቸው። በፍትሕ ሚኒስቴር በኩል ግን ሂደቱ ትናንሽ አሳዎች ላይ ብቻ አያነጣጥርም ቢባልም፣ በተለይም ሂደቱ ከፍተኛ የመንግስት ሹመኞችን፣ ወታደራዊ የጦር መኮንኖችን እና የፖለቲካ ባለስልጣናትን ሊያካትት መቻሉን የሚያነሱም፣ ሂደቱን አብዝተው ይጠራጠሩታል።

* የሽግግር ወቅት ፍትሕ ዐራት ዓላማዎች እንዳሉት ይታመናል። ከእነዚኽ አንዱም፣ ተመሳሳይ ነገር ዳግም እንዳይከሰት ምን አይነት ለውጥ እና ማሻሻያ ያስፈልጋል የሚለውን ከመረዳት ባለፈ፣ መፍትሔው የሕግ እና/ወይም የተቋማት ማሻሻያ ሊሆንም ይችላል። ከዚህ አኳያስ፣ ብዙዎች ይኽ የሽግግር

ፍትሕ አስፈላጊ እንዲሆን ያደረጓቸውን ጥፋቶች የቀሰቀሰው አኹን ያለው ቋንቋ ተኮር የፌደራል ሥርዓት ነው ብለው ይከራከራሉ፤ እናም፣ ጥፋቶቹ እንዳይደገሙ መሠረታዊ ተቋማዊ ለውጥ ይደረጋል የሚለውን የሽግግር ፍትሕ አዕማድ ከያዝን፣ ይኽ የፌደራሉ ቅርጽ ሊቀየር የሚችልበትን እድል ፊት ለፊት አያመጣም የሚሉ ታዛቢዎችም፣ ከፊል ጥርጣሬያቸውን በእንዲኽ መልኩ ባለ መጥይቃዊ ሒሳዊ ትችት ያቀርቡታል።

* የሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ከዓለም ዓቀፍ ጫና እና ማዕቀብ ማምለጫ እና ዓለም ዓቀፍ ማኅበረሰቡን ለማባበል ነው የሚል ክስም በአለፍ ገደም ይደመጣል። ተቺዎቹ ለዚህ ማሳያ የሚያደርጉትም፣ ፖሊሲውን የማርቀቅ ሂደት ከተጀመረ በኋላ ምዕራባውያኑ ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማደስ መጀምራቸውን በማንሳት ነው፤ ለዚኽም ነባራዊ ማስረጃ አድርገው የሚጠቅሱት፣ በትግራይ ተቀስቅሶ ወደ አማራ እና አፋር ክልሎች በተዛመተው የሰሜኑ ጦርነት ወቅት ኢትዮጵያ ላይ በርትቶባት የነበረው ጫና አኹን መለሳለሱን ነው። የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ የማርቀቅ ሂደቱ ከተጀመረ በኋላ የምዕራባውያን አገራት ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማደስ ጀምረዋል የሚሉት ታዛቢ ተቺዎቹ፣ መንግሥት ይሔንን የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ የጀመረው ዓለም ዓቀፍ ማኅበረሰቡን ለማባበል እና የሚመጣውን ጫና ለመቋቋም ነውም ሲሉ ይደመጣሉ።

## የብሪፎ ምክረ ሐሳቦች

ከላይ ከጠቃቀስናቸው ነጥቦች አኳያ፣ ተቋማችን ብሪፎ፣ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው የታሰበለትን አገራዊ ፋይዳ ያዋልድ ዘንድ ጥቂት ተቋማት ተኮር እና ነባራዊነት ይኖራቸዋል ብላ የምታምንባቸውን ምክር-ሐሳቦች እንደወትሮው ማቅረብ ትሻለች።

አስቀድመን፣ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት ይኽንኑ የሽግግር ፖሊሲ እና ተያያዥ ጉዳዮችን አስመልክቶ ሊከውናቸው ይገባሉ ያልናቸውን ሕጋዊ እና ተቋማዊ ግብሮች እንጠቅሳለን።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ከሽግግር ፍትሕ ሂደት ጋር ያለው ግንኙነት እጅግ የጠበቀ እና ወሳኝ ነው። ምንም እንኳን ፖሊሲው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ቢረቀቅም፣ ምክር ቤቱ ሂደቱን ሕጋዊ እና ተዓማኒ ለማድረግ የሚከተሉት ዐራት ዋና ዋና ሚናዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፤

* ሕግጋት እና ሕጋዊ ማዕቀፍ ማበጀት፦

የፍትሕ ሚኒስቴር፣ ከኹለት ዓመታት በፊት ባወጣው የሽግግር ፍትሕ ትግበራ ፍኖተ-ካርታ፣ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው ወደ ተግባር ለመግባት የተለያዩ አዳዲስ ሕግጋት እንደሚወጡ ይዘረዝራል። ለማስታወስ ያህልም፥

* የሽግግር ፍትሕ ተቋማት ማቋቋሚያ ዐዋጆች፤
* ልዩ ችሎት ማቋቋሚያ ዐዋጅ፤
* የሽግግር ፍትሕ ልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋም ማቋቋሚያ ዐዋጅ፤
* ክሶችን የመስማት እና ውሳኔ የመስጠት ተግባራትን የሚያከናውን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ልዩ ችሎት ማቋቋሚያ ዐዋጅ፤
* የሕግ እና ተቋማዊ ማሻሻያ ሥራዎችን የሚያከናውን ኮሚሽን ማቋቋሚያ ዐዋጅ፤

* የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋምን አደረጃጀት፣ ስልጣን እና ተግባራትን የሚደነገግ ዐዋጅ፤
* የእውነት ማፈላለግ/ማውጣት፣ የእርቅ፣ ምህረት እና ማካካሻ ኮሚሽን ማቋቋሚያ ዐዋጅ፤
* እንዲኹም የኮሚሽኑን ሥልጣን፣ ተግባራት እና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚደነገግ ዐዋጅ፤

የሚሉትን በዋናነት መጥቀስ ይቻላል። በዚኽ ጉዳይ ላይ ያለን አስተያይትም፣ ምንም እንኳን አንዳንዶቹ ዐዋጆች በረቂቅ ደረጃ እንደነበሩ ብንረዳም፣ የእነዚኽ ዐዋጆች እስከ ዛሬ አለመውጣት፣ የሽግግር ፍትሑ ዘገየ አልያም ከፋ ካለ አይካሄደም ለሚለው ትችት እጅጉን ሰፊ በር ከፍቷልና፣ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የቀሩት ወራት ሳይጠናቀቁ ዐዋጆች የሚጸድቁበትን መፍትሔ ቢሻ፣ ከላይ አጠር አድርገን የጠቅስናቸውን ትችቶች ጭምር ይፈታልና ቢታሰብበት የሚል ነው።

* በፍትሕ ሚኒስቴር አማካኝነት የወጣው ፎኖተ-ካርታ፣ በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው ላይ የተመላከቱ ተቋማት በሕግ እስኪቋቋሙ እና ኃላፊነቶቻቸውን ሙሉ ለሙሉ እስኪረከቡ ድረስ ባለው የጊዜ ማዕቀፍ የሚከናወኑ የትግበራ ሥራዎችን የሚከታተል እና የሚያስተባብር፤ እንዲኹም በፖሊሲው ላይ የተመላከቱ አዳዲስ የሽግግር ፍትሕ ተቋማት ከተቋቋሙ በኋላ አጠቃላይ የትግበራ ሂደቱን አፈፃፀም በዘላቂነት የሚያስተባብር እና የሚከታተል የሽግግር ፍትሕ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ የተሰኘ መድረክ እንደሚቋቋም ደንግጓል። አደረጃጀቱም፣ ከሌሎች ተቋማት በተጨማሪ፣ ከእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ኹለት እንደራሴዎች እንደሚኖሩበት አስቀምጧል፤ ከዚኽ አንጻርም፣ ብሪጅ የእነዚኽ ኹለት እንደራሴዎች አመራረጥ እጅጉን በሰላ እና ቢቻል ኹሉም እንደራሴዎች የተሰማሙባቸው እና በሙሉ ድምጽ ድጋፍ ያገኙባቸው ይሆኑ ዘንድ፣ ምክር ቤቱ ጠበቅ ያለ ሥራ ይሠራ ዘንድ ብሪጅ ማሳሰብ ትሻለች።
* ሌላው የብሪጅ ምክር-ሐሳብ የሚያጠነጥነው፣ በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው ላይ ይቋቋማሉ በተባሉት ተቋማት ዙሪያ ነው። ይኽም ማለት፣ የሽግግር ፍትሑ መሳካት እና ሕዝባዊ ተዓማኒነት በእነዚኽ ተቋማት ገጽታ ላይ መንተራሱ አሌ አይባልም። እንደሚታወሰው፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን በመጡ ማግስት የተቋቋሙት የዕርቀ ሰላም እና የአስተዳደር ወሰን እና ማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን መሬት የወረደ ሥራ ሳይሰሩ በሕግ የተሰጣቸው የሥራ ዘመን ተጠናቋል። ከዚኽ አንጻርም፣ በቀጣይ የሚቋቋሙት የሽግግር ፍትሕ ትግበራውን የሚያሳልጡ ተቋማት፣ መሰል ዕጣ ፈንታ እንዳይጎበኛቸው፣ እንደራሴዎቹ ብርቱ ጥንቃቄ ያደርጉ ዘንድ ብሪጅ አገራዊ ጥሪዋን ማስተላለፍ ትሻለች። ስለምን ቢሉ፣ በተደጋጋሚ የሽግግር ኮሚሽኖች መቋቋማቸው በንድፈ ሃሳብ ደረጃ የወደፊት የሽግግር ሂደት ተነሳሽነቶች ቅቡልነት እንዳይኖራቸው ሊያደርግ ይችላልና።
* በፍኖተ-ካርታው ላይ እንደተጠቀሰው፣ ልዩ ፍርድ ቤትን ለማቋቋም የተጠቀሱት ምክንያቶች አሳማኝ ቢሆኑም የልዩ ፍርድ ቤት ሕገ-መንግሥታዊነት በአግባቡ ሊታይ የሚገባ ይመስለናል። በዚኽ ረገድ፣ “የዳኝነት ሥልጣንን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በሕግ የመዳኘት ሥልጣን ከተሰጠው ተቋም ውጭ

የሚያደርግ፣ በሕግ የተደነገገን የዳኝነት ሥርዓት የማይከተል ልዩ ፍርድ ቤት ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም።›› የሚለውን፣ የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት ዐንቀጽ 78(6) መሠረት በማድረግ ልዩ ፍርድ ቤት ሕገ-መንግሥታዊ አይሆንም የሚል ክርክር ሊነሳ ይችላል የሚል ስጋት አለን። እንደ ተቋማችን መረዳት፣ ይኽ የሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ ሊታይ የሚገባው ከመነሻው እና ድንጋጌው ከወጣበት አውድ አንፃር ነው። ያም ቢሆን ግና፣ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ዐዋጁን ሲያጸድቅ ለዚኽ መሰሉ መከራከሪያ ዓይነተኛ ምላሽ የሚሰጥ ማብራሪያም ሆነ የዐዋጅ ድንጋጌ ክፍል የሚካተትበትን ኹኔታ ግንዛቤ ውስጥ ቢያስገባ፣ ከማይጠቀም ሙግት ሂደቱን ማትረፍ ይቻላል ብለን እናምናለን።

* ሌላይኛው የብሪጅ ዋነኛ የምክር-ሐሳብ ማጠንጠኛ፣ የሽግግር ፍትሑን ይመራሉ፤ ያስፈጽማሉ የተባሉትን እና ምክር ቤቱ በዐዋጅ ያቋቁማቸዋል ተብሎ የሚጠበቁትን ተቋማት ተቋማዊ ነፃነትን ይመለከታል። የሽግግር ፍትሕ ሂደቱን የሚመሩት ተቋማት (ለምሳሌ የእውነት መፈለጊያ ኮሚሽን ወይም ልዩ ፍርድ ቤቶች) ከሥራ አሥፈጻሚውም ሆነ ከየትኞቹም የፖለቲካ ቡድኖች ተጽዕኖ ነፃ መሆን እንዳለባቸው ዕሙን ነው።

  የእንደራሴዎቹ ምክር ቤትም፣ የእነዚኽን ተቋማት አመራሮች በመሾም እና አሠራራቸውን በመቆጣጠር፣ ሂደቱ በየትኞቹም የፖለቲካ ኃይሎች እንዳይጠለፍ ብርቱ ተቋማዊ ቁጥጥር የማድረግ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነት አለበትና ለዚኽ የሚሆኑ ውስጣዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋማቱን በባለሙያውም ሆነ በሎጀስቲክስ አስቀድሞ እንዲያጠናክር ብሪጅ ማስታወስ ትሻለች።

* መጥቀስ እንደማያሻውም፣ እነዚኽ ብርቱ ጥንቃቄ ይደረግባቸው ያልናቸው ተቋማት፣ ምክር ቤቱ በሚሾማቸው ተሿሚዎች የሚመሩ ናቸው። ከዚኽ አንጻርም፣ እንደራሴዎቹ የተሿሚዎቹን ገለልተኝነት በበዛ ጥንቃቄ ያደርጉ ዘንድ ተቋማዊ አደራችንን መጥቀስ እንሻለን፤ ምክንያቱም፣ የእነዚኽ ተቋማት መሪዎች በአንድ አካል ፈቃድ ላይ ተንተርሰው ከተሾሙ፣ ነገር-ዓለሙ ኹሉ "የአሸናፊዎች ፍትሕ" ተደርጎ ሊወሰድ ይችላልና። ይኽ የብሪጅ የአደራ ማስታወሻ በኮሚሽነሮቹ ብቻም ላይ ሳይሆን በልዩ ችሎቶቹ በሚቀመጡት ዳኞች ላይም ጭምር ነው።

* የሽግግር ፍትሕ ሂደት፣ ሊገመቱ የሚከብዱ ዓመታትን እንደመፈለጉ፣ ከአገር ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ፕሮጀክት ነው። ለተበዳዮች ካሳ ለመክፈል፣ ለምርመራ ሂደቶች እና ለተቋማት ግንባታ የሚውለውን በጀት የሚፈቅደው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት መሆኑም ግልጽ ነው፤ ከዚኽ አንጻርም፣ አገሪቷ ካላት ካዝና ውስጥ ለዚኽ ፍይዳው ለበዛ ሂደት የምትመድበው ገንዘብ ካለአንዳች ሽርፍራፊ ለታሰበለት ዓላማ መዋሉን ምክር ቤቱ በበረታ ተቋማዊ ቁጥጥር ሊክወነው የሚገባ ተግባር መሆኑን ማስታወስ እንሻለን።

* ከዚኹ የምክር ቤቱ የተቋማት የቁጥጥር ሕገ-መንግሥታዊ ኀላፊነቱ ሳንወጣ በተያያዥ መጥቀስ የሚያስፈልገው ምክረ-ሐሳባዊ ነጥብ፣ እንደራሴዎቹ ሙሉ የሽግግር ፍትሕ ሂደቱን የመቆጣጠር ሕጋዊ ኀላፊነታቸው ነው። ይኽም ማለት፣ የሽግግር ፍትሕ ሂደቱ በታቀደለት መንገድ እየሔደ መሆኑን፣ ሰብዓዊ

መብቶች መከበራቸውን እና ለተጎጂዎች ፍትሕ እየተሰጠ መሆኑን እንደራሴዎቹ በሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎቻቸው በኩል በየጊዜው ሪፖርት እየተቀበሉ ጠንካራ ክትልል ማድረግ ይኖርባቸዋል እንላለን። በተለይም የፍትሕ ሂደቱ ተበዳዮችን ማዕከል ማድረጉን የማረጋገጡን ጉዳይ አበክረው ይመለከቱት ዘንድ ዜግነታዊ ጥሪያችንን ማሰማት እንሻለን።

* ሌላው የምክረ-ሐሳባችን መሸከርከሪያ ሕገ-መንግሥታዊ ተጣጣሚነት ላይ ያተኮረ ነው፤ የሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ከአገሪቱ ሕገ-መንግሥት ጋር እንዳይጋጭ (ለምሳሌ ያህልም፣ አንድን ወንጀለኛ ያለ መደበኛ ፍርድ ቤት በሽግግር ፍትሕ ማዕቀፍ ብቻ ማየትን አልያም በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ሊጠየቅ የሚችልን እንደራሴ ያለመከሰስ መብት የማንሳትን የመሳሰሉ ጉዳዮችን) የመከላከል ሥልጣኑ በዋናነት በዚኹ ምክር ቤት ላይ ያረፈ ነውና፣ ይኽ ሕገ-መንግሥታዊ ነጥብም አስቀድሞ አትኩሮት ይሰጠው ማለት እንሻለን።

ከእነዚኽ እንደራሴዎቹ ተኮር ምክረ-ሐሳቦቻችን ባሻገር፣ ራሱን የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲውን እና የአተገባበር ፍኖተ-ካርታውን አስመልክቶ ኹለት ነጥቦችን አክለን ማንሳት እንሻለን፤ እነዚኽም፥-

* የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው፣ የሽግግር ፍትሑ ተፈጻሚ የሚሆነው በመላ አገሪቱ እንደሆነ ያትታል። ይሁንና፣ በሰሜኑ ጦርነት ወቅት በትግራይ ሕዝብ ላይ የኤርትራ ወታደሮች በከባድ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት እና የጦር ወንጀል ሊያስብሉ የሚችሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን መፈጸማቸውን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ በዚኹ ወር በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በነበራቸው የ2018 በጀት ዓመት የስድስት ወራት የመንግሥታቸው የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ወቅት ማንሳታቸው ይታወቃል።

ከ'ርሳቸው በተጨማሪም፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ዋና ኮሚሽነር ማረጋገጣቸው ይታወሳል። ከዚኽ አኳያም፣ በከባድ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የተሳተፉ የኤርትራ ወታደሮች ጉዳይ በሌሉበትም ቢሆን በሚቋቋመው ልዩ ፍርድ ቤት ሊታይ እና ተጠያቂነታቸውም ሊረጋገጥ ይገባል እንላለን። ከዚኽ ባለፈም፣ በሚቋቋመው የእውነት አፈላላጊ ኮሚሽን አማካኝነትም በእነዚኹ የውጭ ኃይሎች የተፈፀሙ ከባድ ወንጀሎች ይፋ ሊደረጉ እና ሃቆቹም ሊሰነዱ ይገባል እንላለን።

* ሀገር በቀል የግጭት አፈታት ዕሴቶችን ጥቅም ላይ በማዋል ረገድ፣ በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው እና በፍኖተ-ካርታው ላይ መጠቀሳቸውን በእጅጉን በአዎንታዊነት እንመለከተዋለን። ያም ሆኖ፣ ትግበራው በክልሎች እና በወረዳዎች ደረጃ በሚፈፀምበት ወቅት ሰብዓዊ መብቶችን ያማከለ እና የተጎጂዎችን፣ በተለይም የሴቶችን፣ የሕጻናትን እና የአካል ጉዳተኞችን ሕገ-መንግሥታዊ ጥበቃ ባማከለ መልኩ ተግባራዊ እንዲደረጉ ልዩ ትኩረት እና ክትትል ሊደርግባቸው እንደሚገባ ማስታወስ እንሻለን። በዚኽ ረገድ፣ እንደ ብሪጅ መሰል የሲቪል ማኅበረሰብ ተቋማት ቀዳሚ ሚና እንደሚኖራቸው የሚሳተፉበትን ማዕቀፍ አስቀድሞ ማበጀት ጠቀሜታው ብዙ ነው ማለት እንሻለን።

## ፍካሬ ዘ እንደራሴ

"እንደራሴ" የሚለው ንባበ-ቃል በኢትዮጵያ ጥንታዊ እና ዘመናዊ የፖለቲካ ተዋስዖ እና የሥነ-መንግሥት ታሪክ ውስጥ ግዝፈት የነሳ ፍካሬያዊ ንባበ-ቃል ነው። የቃሉ ከየት መጥነት እና ፍካሬም፣ በአጠቃሎ መልኩ ይኽን መሰል ፍቺዎች ነበሩት/አሉትም።

ንባበ-ቃሉ የተገኘው "እንደ" እና "ራሴ" ከሚሉ የኹለት ቃላት ጥምረት ነው። "እንደ"፦ መስያ፣ ፈንታን ወይም ምትክን ሲያመለክት፤ "ራሴ"፦ ራስ ጠሪውን ማንነት አልያም ባለቤቱን-ሲፈከርም ባለሥልጣኑን ያነጽራል። በአማሪያዊ ፍቺውም፣ "እንደ እኔ" ወይም "እኔን ሆኖ" ማለት ነው ይሏል። በኢትዮጵያ ሥነ-መንግሥት ታሪክ "እንደራሴ" የሚለው ማዕረግነቱን ሲያጣቅስ፣ በተለያዩ ዘመናት የተለያየ ማኅበረ-ፖለቲካዊ ትርጓሜ ነበረው፤ ለማሳያ፦

ሀ- የንጉሠ ነገሥቱ ተወካይ (በፈረንጅ አፍ- Regent እንዲሉ)፦ በንጉሣዊው ሥርዓት ዘመን ንጉሠ ነገሥቱ በአንዳች ምክንያት (ለዐቅመ-መንበር ባለመድረስ፣ በሕመም ወይም በሌላ ምክንያት) አገረ-መንግሥቱን መምራት ካልቻሉ፣ ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቶት አገሪቱን የሚያሥተዳድረው ሰው "ቢትወደድ-እንደራሴ" ይባል ነበር።

ለ- የአካባቢ ወይም የክፍለ-ሀገር ገዢነት፦ ንጉሠ ነገሥቱ በየክፍለ ሀገራቱ 'ራሳቸው ዘወትር መገኘት ስለማይችሉ፣ በ'ርሳቸው ስም የሚፈርዱ እና የሚያሥተዳድሩ ተወካዮቻቸውን "እንደራሴ" ይሏቸዋል፤ ይኽም የንጉሡ ምሉዕ ተወካይነትን ይሰጣል።

ሐ-የሕዝብ እንደራሴነት፦የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ከመጣ ወዲኽ ግን ቃሉ አዲስ ፍካሬ ያዘ። ሕዝቡ በ'ራሱ ፈንታ ሆኖ በምክር ቤት እንዲመክርለት እና ውሳኔም እንዲሰጥለት የሚመርጣቸው ሰዎች "የሕዝብ እንደራሴዎች" መባል ጀመሩ። የዚኽ ፍካሬም፣ "ሕዝቡን ሆኖ የሚሠራ"፣ "ምስለ-ሕዝብ" አልያም "የሕዝቡ ተወካይ" የሚል ትርጓሜን አሰጠው።

ዛሬ "ተወካይ" (በምዕራቡ የምክር ቤት ታሪክ ጅማሮ-Representative-እንዲሉ) ከሚለው ቃል ጋር መሳ ለመሳ ሆኖ ያገለግላል። ሆኖም "እንደራሴ" የሚለው ቃል ከውክልና ባለፈ፣ የወከለውን አካል ሙሉ ክብር እና ማንነታዊ ተዛምዶ ይዞ የሚገኝ ክብደት ያለው ፖለቲካዊ እና ማኅበረ-ባህላዊ ፍካሬ አለው።

## የብሪጅ አፈካከር

ተቋማችን ብሪጅ፣ የአማርኛን ሰዋስው ደንብ ጠብቃ፣ ይኽንን ቃል ከኋለኛው ወደዚኽ ዘመን አናጥቃ በመፈከር ተጠቅማለች። አስቀድመን ሊቃውንቱ ያስቀመጡትን እንጥቀስ፤ ደስታ ተክለ ወልድ፣ እንደ ራሴ፣ እኔን ሆኖ፣ የእኔን ሥልጣን ይዞ የሚሠራ ብለው ሲፈቱት፤ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ በፈንታ፣ በምትክ የሚቆም ሲሉት፤ ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጸው በተራቸው፣ ተለዋጭ፣ ተወካይ፣ ባለሙሉ ሥልጣን የሚል ፍቺ ይሰጡታል። ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀልም ቢሆኑ፣ አንድ ሰው በራሱ ስም ሳይሆን በሌላው ስም ተገኝቶ የሕግ ተግባራትን ሲያከናውን እንደራሴ መባሉን ያነሳሉ። እነዚኽ ዋቢዎች እንደሚያሳዩት፣ ቃሉ በመጀመሪያ ለነገሥታት ተወካዮች ብቻ ይሠራበት የነበረ ሲሆን፣ ኋላ ለሕዝብ ተወካዮች እንዲሠራበት የተደረገው የሕዝቡን ልዕልና ለመግለጽ ውለዋል፤ አለፍ ሲልም፣ ተወካዩ ሕዝቡን ሆኖ ይገኛል፤ እንደ ሕዝቡ ሆኖ ይጠራል የሚለውን ፍካሬ ይሰጣሉ።

በዚኽ አግባብ፣ "እንደራሴ" ስንል፦ አንድም ራስ የሚለውን የኢትዮጵያ ፌዴሬሽን ከቆመበት 'የራስን ዕድል በራስ የመወሰን' ሕገ-መንግሥታዊ ነባር መርህ ጋር አናጽረን ፈክረነዋል። ይኽ ማለት፣ በዚኽ መርህ ውስጥ ያለው 'ራስ'፣ የሚለው ትርጉም የሚጠቅልላቸውን ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፣ በ "እንደራሴ" ውስጥ ያለውን 'ራሴ'ን ለመፍታት ፍካሬያዊ ትርጓሜን ተጠቅመናል። ከዚያ ባለፈም፣ በቀደመው ዘመን መራጩ ንጉሠ ነገሥቱ እንደሆነው ሁሉ፣ በዚኽኛው የእኛው ዘመን ሕዝብ ነውና፣ "እንደራሴ" ስንል፦ እንደ መረጠው ሕዝብ፣ ብሔረሰብ አልያም ብሔር የሆነ በሚል ፍቺ መጠቀማችንን ልብ ይሏል። በዘመናዊው የምርጫ ሥርዓት ስናነጽረውም፣ መራጩ ግለሰብ እንደራሴውን 'ተናገር በከንፈሬ፣ ተቀመጥ በመንበሬ' ሲል፣ በነገረ-ሕይወቱ ይወስንለት ዘንድ ወደ ምክር ቤቱ መርጦ ይልከዋል። የመረጠውም እንደራሱ ካልሆነለት፣ ምስለ እኔነቱን ሊነጥቀው መቻሉን ያስረግጣል።

የ"እንደራሴ" ንባበ-ቃል፣ ምንም እንኳን የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የእንደራሴዎች ምክር ቤት ሲቋቋም፣ የምክር ቤቱ የሥራ ቋንቋ በዘመኑ ብሔራዊ ቋንቋ የነበረው አማርኛ ብቻ ቢሆንም ቅሉ፣ ንባበ-ቃሉ ግን በሌሎቹ የአገራችን የብሔር ብሔረ ሰቦች ቋንቋዎች ውስጥም መገኘቱን ልብ ይሏል፤ ለማሳያ፦ በሲዳማ- amaalete mina፣ በአፋን ኦሮሞ-Bakka bu'aa፣ በትግሪኛ- ከማይ፣ በወላይተኛ Kal Ati-ya/Taga ton መባሉን ያስታውሷል።

**ከራስ ውርድ፦**

"በእነዚኽ ወርኃዊ የእንደራሴዎቹ ጥቅንሮች ውስጥ ያሉት ኹሉም የገጸ-ሰብ እና የገጸ-መስኮች ምስሎች የተገኙት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ይፋዊ የመረጃ ምንጮች ነው፤ እንዲኹም፣ ኹሉም ቁጥራዊ ዘገባዎች የተወሰዱትም ከዚኽ ምንጭ ነው። ዳሰሳዊ ምልከታዎቹ፣ አጠቃሎዎች እና ተያያዥ ትንታኔዎቹ የተቋማችን ናቸው።"

# እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

BRIDGE Research & Innovation for Democratic Governance and Enhanced Peace

+251 115 57 74 96

+251 99 808 5013

info@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, O ce No. 5, Addis Ababa.